# ጥሪ ወደ ሶላት!!!

*ሀያ አለ ሶላህ!!!*

ዝግጅት፦ ኻሊድ አቡ ሷሊህ

ትርጉም፡- ኒዛሙዲን አወል (አቡ አይመን)

## حيّ على الصلاة

إعداد: خالد أبو صالح

ترجمة: نظام الدّين أوّل

أمهري – إثيوبيا

# ማውጫ


ኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር ..... 3
የአሳታሚው መቅድም ..... 4
የተርጓሚው መቅድም ..... 5
የሶላት ደረጃ እና ቱርፋቱ ..... 7
አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ!! ..... 16
ሰዎች ከሶላት አንጻር ያላቸው ደረጃ ..... 22
የሶላትን ልቅና የምናገኝበት መንገዶች ..... 24
ተቀባይነት ያለው ሶላት ..... 25
ሰለፎች ከሶላት ጋር የነበራቸው ቁርኝት ..... 31
ሰለፎች በሶላት ውስጥ የነበራቸው ኹሹዕ ..... 33
በሶላት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ..... 35
  የጀመዓ ሶላት ..... 35
  የጁምዓ ሶላት ..... 37
  የተራዊህ ሶላት ..... 38
  የዒድ ሶላት ..... 39
  የሶላቱል ጀናዛ አሰጋገድ ..... 41
  የመንገደኛ አሰጋገድ ..... 42
  የማይሰግድ ሰው ሁክም ..... 43
  የተለያዩ ርዕሶች ..... 44
نبذة تعريفية عن مركز ابن مسعود الإسلامي ..... 50

# ኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር

በሰኔ ወር 2001ዓ.ል ተመስርቶ በተቀናጀ መልኩ ለሙስሊሙ ሕብረተሰብ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው።

<u>የማዕከሉ ዋና ዋና ክፍሎች</u>

- የዓረብኛ ቋንቋና የሸሪዓዊ ጥናቶች ኢንስቲትዩት (ለሴቶች)
- የሙሉ ቀን የቁርዓን ሒፍዝ መጅሊስ (ለሴቶችና ለወንዶች)
- ኢስላማዊ የቤተ መፃህፍት አገልግሎት
- የህፃናት ኢስላማዊ የተርቢያ ማዕከል
- የመድረሳዎች ድጋፍ መስጫ እና የካሪኩለም ማሻሻያ
- የኢንተርኔት ዳዕዋ ማዕከል
- መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ ትምህርት
- ሙስሊም ላልሆኑና በቅርቡ ለሰለሙ መሰረታዊ ትምህርት
- ለዲን ተማሪዎች መደበኛ ያልሆነ የአካዳሚ ትምህርት
- የተለያዩ ኪታቦች ቂራዓት ለወንዶችና ለሴቶች
- የተለያዩ ኮርሶች፣ ሴሚናሮች እና ኮንፈረንሶች
- የካሴቶች፣ ሲዲዎችና የተለያዩ በራሪ ወረቀቶች ስርጭት
- የመስጅዶች ግንባታ
- የኡስታዞች ድጎማ
- የወቅፍ ማስተባበርያ

**<u>የማዕከሉ አድራሻ</u>**
☏ +251112781893
Fax: +251112779660
e-mail:-info@nesiha.org
www.nesiha.org
<u>አዲስ አበባ</u>
<u>ኢትዮጵያ</u>

# የአሳታሚው መቅድም

የኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር ከተመሠረተበት ዓላማ አንዱ **ቁርአንና** ትክክለኛ **ሀዲስን** መሠረት ያደረጉ ኢስላማዊ መፃህፍትን በሀገራችን በሰፊው በሚነገሩ ቋንቋዎች በማዘጋጀትና በመተርጎም ማ ቅረብ ሲሆን፤ ይህንንም **ጥሪ ወደ ሶላት!!!** የሚል ርዕሥ ያለውን መፀሃፍ ለአንባቢያን ሲያቀርብ ታላቅ ደስታ ይሰማዋል:: አንባቢያን በመፅሃፉ ዙሪያ ያላቸውን አስተያየት እንዲጠቁሙ እየጠይቅን ባወቅነው የምንጠቀም ያደርገን ዘንድ አላህን እንለምነዋለን::

# የተርጓሚው መቅድም

## በአላህስምእጅግበጣምሩህሩህበጣምአዛኝበሆነው፡፡

ምስጋና ለአለማት ጌታ፤ ያ ሁሉንም በልክ ለፈጠረው፤ ከፈጠረም በኋላ መመሪያን በማውረድ በምድር ላይ ስርዓትን ላስተማረው አላህ ተገባው ፡፡ የአላህ ሶላትና ሰላም የመልዕክተኞች እና የነብያቶች መሪ በሆኑት በነብዩ ሙሀመድ ﷺ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን ፡፡

ሶላት ከስራዎች ሁሉ በላጭ፤ የትንሳዔ ቀን በመጀመሪያ የሚመረመር፤ ለሁሉም ስራዎች ተቀባይነት ወሳኝ የሆነ የኢባዳ አይነት ነው ፡፡ ሶላት በኢስላም ይህ ነው የማይባል ስፍራ ቢኖረውም በብዙ ሙስሊሞች ዘንድ ተገቢውን ደረጃ ሲያገኝ አይስተዋልም ፡፡ በመሆኑም ከሶላታቸው የሚዘናጉ ብሎም የሚተው በርካታ ሙስሊሞችን ማየት እንግዳ አይደለም ፡፡ የዚህም ዋነኛው ምክንያት የዕውቀት እጥረት በመሆኑ፡ - የማህበረሰቡን እውቀት በማጎልበት ሶላት በኢስላም ያለውን ደራጃ ማስገንዘብ ተገቢ ነው ፡፡ ከዚህ አንጻር ሁሉም ያአቅሙን ያህል ሀላፊነቱን መወጣት አለበት ፡፡ ኢስላማዊ ግዴታውም ነው ፡፡ የዚህም መጽሐፍ አላማ ይኸው ነው ፡፡

ይህ መጽሐፍ ስለ ሶላት ደረጃና ጥቅም የሚያትተው *“ሀያ አለ ሶላህ”* በሚል ርዕስ በሸይኽ ኻሊድ አቡ ሷሊህ በአረብኛ ቋንቋ የተጻፈው መጽሐፍ ትርጉም ነው ፡፡ መጽሀፉም ሶላት በኢስላም ያለውን ደረጃ፤ ጥቅሙን፤ የማይሰግድ ሰው የሚጠብቀውን እጣ ፈንታ፤ የሰጋጆችን የተለያዩ ገጽታዎች እና ተቀባይነት ያለው ሶላት ምን መምሰል እንዳለበት የሚያትት ዝርዝር ነጥቦችን አካቶ ይዟል ፡፡ በተጨማሪም በሶላት ዙሪ የሚያጠነጥኑ ጥያቄዎችን እና በተለያዩ እውቅ ኡለሞች የተሰጡትን መልሶቻቸውን

ለአንባቢው ይረዳ ዘንድ አክዬበታለሁ ::

በጨረሻም ይህን ጽሑፍ ለአንባቢያን ጠቃሚ እንዲያደርገውና እኔንም ከምንዳው ተቋዳሽ ያደርገኝ ዘንድ ፈጣሪዬን አላህ እየለመንኩ፤ የአንባቢያን ገንቢ አስተያየት እንዳይለየኝ እጠይቃለሁ ::

ኒዛሙዲን አወል (አቡ አይመን)
ረመዳን 1431 ዓ.ሂ
E-mail:- rehu2000@gmail.com, nizawol@yahoo.com

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ለአለማት ጌታ ምስጋና ተገባው ። አላህ ሆይ የመጀመሪያዎቹም የመጨረሻዎቹም መሪ በሆኑት በነብያችን ሙሀመድ ﷺ በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በሁሉም ባልደረቦቻቸው ላይ ፣ ሶላትን እና ሰላምን አውርድ ።

ሶላት በኢስላም ከፍ ያለ ደረጃና የላቀ ስፍራ አለው ። ራስ የአካል ቁንጮ እንደሆነው ሁሉ ሶላትም የኢስላም ቁንጮ ነው ። አካል ያለ ራስ መኖር እንደማይችለው ሁሉ እስልምናም ያለ ሶላት አይመሰረትም ።

## የሶላት ደረጃ እና ቱርፋቱ

1. *ሶላት የተደነገገው መልዕክተኛው* ﷺ ሰማይ በወጡበት ሌሊት (*በለይለተል ሚዕራጅ* ) እዚያው ሰማይ ላይ ሲሆን ሌሎች ኢባዳዎች ግን (የተደነገጉት ) በምድር ላይ መሆኑ የሶላትን የላቀ ክብርና ደረጃ አመላካች ነው ።
2. ሶላት፡- ብቸኛው በቀን አምስት ጊዜ በመደጋገም የሚተገበር የኢስላም ማዕዘን ነው ። በወር አበባና በወሊድ ደም ጊዜ በስተቀር በምንም መልኩ ተፈጻሚነቱ የጸና ነው ።
3. ሶላት፡- ከስራዎች ሁሉ በላጭ፣ እጅግ ያማረና አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሆነ መለኮታዊ ትዕዛዝ ነው ። ነቢዩም ﷺ እንዲህ በማለት ገልጸውታል ።

«**أفضل الأعمال الصلاة على وقتها**» [متفق عليه]

*"ከስራዎች ሁሉ በላጩ፣ ሶላትን በወቅቱ (በጊዜው) መስገድ ነው ።"*[1]

«**استقيموا ولن تُحْصوا، واعلموا أن خير أعمالكم الصلاة، ولن يُحافظ على الوضوء إلا مُؤمن**» [رواه أحمد والحاكم وصححه الألباني]

---

[1] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

*“በሀቅ ላይ ፅኑ፤ ሁሉንም ስራ ልታሟሉ አትችሉም። ከስራዎቻቹህ ሁሉ በላጩ ሶላት መሆኑን እወቁ። ዉዱዕን (ትጥበትን) አይጠባበቅም ሙዕሚን (አማኝ) የሆነ እንጂ።”*[1]

4. *ሶላት፡-* **የእስልምና ምሰሶ፤ የእምነት ጥንካሬ መሰረት፤ የአማኞች የአይን ማረፊያ ነው። መልዕክተኛው ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-**

«**رأس الأمر الإسلام، وعموده الصلاة، وذروة سنامه الجهاد في سبيل الله**» [رواه أحمد والترمذي وصححه الألباني]

*“የነገሮች ሁሉ ዋናው (ራስ) ኢስላም ነው። ምሰሶው ሶላት ሲሆን ጉልላቱ በአላህ መንገድ ላይ መታገል ነው።”*[2]

5. *ሶላት፡-* **የሙስሊምነት ማስረጃ፤ የአማኝነት ምልክት፤ ነፍስ ጥቡቅ የምትሆንበት (ክብርን የሚያጎናፅፍ) ተግባር ነው። ለዚህም አላህ እንዲህ ይላል፡ -**

﴿فَإِن تَابُواْ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَوُاْ ٱلزَّكَوٰةَ فَإِخۡوَٰنُكُمۡ فِي ٱلدِّينِۗ﴾ التوبة: ١١

*«ንሰሃ በመግባት (ወደ አላህ ከተመለሱ)፤ ሶላትን (ደንቡን ጠብቀው) ከሰገዱ፤ ዘካንም (በአግባቡ) ከሰጡ የእምነት ወንድሞቻችሁ ናቸው።”*[3]

6. *ሶላት፡-* **የታማኝነት ምልክት፤ ንፍቅናን የሚያጸዳ ተግባር ነው። ይህን በማስመልከት መልዕክተኛው ﷺ እንዲህ ብለዋል፡ -**

«**من صلى لله أربعين يومًا في جماعة، يدرك التكبيرة الأولى، كتب له براءتان: براءة من النار، وبراءة من النفاق**» [رواه أحمد وصححه الألباني]

[1] አህመድ እና ሀኪም ዘግበውታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።
[2] አህመድ እና ቲርሚዚይ ዘግበውታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።
[3] አት-ተውባህ፡-11

*“አርባ ቀን በተከታታይ የመጀመሪያውን ተክቢራ (ተክቢረተል ኢህራም ) ሳያመልጠው በጀምዓ ለአላህ ብሎ የሰገደ፤ አላህ ከሁለት ነገሮች ነጻ መሆኑን ይጽፍለታል ። ከዕሳት ነጻ መሆኑን እና ከኒፋቅ ነጻ መሆኑን ።”*[1]

7. *ሶላት፡-* የተከበረና በላጩ ኢባዳ፤ በጣም ትርፋማ ስራ፤ አላህን ይበልጥ እንድንፈራውና ይበልጥ እንድንተናነስለት የሚያደርግ መለኮታዊ ትዕዛዝ ነው ። የሚከተለው የነቢዩ ﷺ ንግግር ይህን ሀሳብ ያጠናክረዋል ።

«الصلاة خير موضوع، فمن استطاع أن يستكثر فليستكثر» [رواه أحمد وحسنه الألباني]

*“ሶላት በላጩ ኢባዳ ነው ። በብዛት መስገድን የቻለ ያብዛ ።”*[2]

8. *ሶላት፡-* ቸርና ሩህሩህ የሆነው ጌታ ትዕዛዝ፤ የምርጡ ነብይ ኑዛዜ፤ የሙስሊሞችና የሙዕሚኖች መገለጫ ምልክት ነው ። አላህም ይህን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡-

﴿حَٰفِظُواْ عَلَى ٱلصَّلَوَٰتِ وَٱلصَّلَوٰةِ ٱلۡوُسۡطَىٰ وَقُومُواْ لِلَّهِ قَٰنِتِينَ ٢٣٨﴾ البقرة: ٢٣٨

“(አምስት ወቅት ) ሶላቶችን በተለይም የመካከለኛዋን ሶላት (በጊዜውና በተሟላ ስርዓት ) አዘውትራችሁ ፈጽሟቸው ። ለአላህ ታዛዦች ሆናችሁም ቁሙ ።”[3]

﴿وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ لِذِكۡرِيٓ ١٤﴾ طه: ١٤

*‹‹ለኔ ማስታወስም ሶላትን በአግባቡ ስገድ ።››*[4]

---

[1] *አህመድ ዘግበታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።*
[2] *አህመድ ዘግበታል። አልባኒ ሀሰን ብለውታል።*
[3] *አል-በቀራ፡* 238
[4] *ጣሃ፡-*14

9. *ሶላት፡- ደረጃን ከፍ የሚያደርግ፤ መጥፎ ነገርን የሚያስወግድ፤ ከወንጀል የሚያነጻ ተግባር ነው ። የሚከተሉት የነቢዩ ﷺ ሀዲሶች ለዚህ ማስረጃ ናቸው ።*

«**أرأيتم لو أن نهرًا بباب أحدكم، يغتسل منه كل يوم خمس مرات. هل يبقى من درنه شيء**» قالوا: لا يبقى من درنه شيء. قال: «**فذلك مثل الصلوات الخمس يمحو الله بهن الخطايا**» [متفق عليه]

*"እስኪ ንገሩኝ በአንዳችሁ ደጃፍ ወንዝ ቢኖርና በቀን አምስት ጊዜ ገላውን ቢታጠብ ከእድፉ ይቀራልን ?" እነሱም አሉ፡ - ምንም ከእድፉ አይቀርም ። እሳቸውም አሉ፡ - "ይህ የአምስት ወቅት ሶላቶች እና አላህ በሰላት ከወንጀል እንዴት እንደሚያጸዳ የሚያሳይ ምሳሌ ነው ።"*[1]

«**ما من امرئ مُسلم تحضره صلاة مكتوبة، فيُحسن وضوءها، وخشوعها، وركوعها، إلا كانت كفَّارة لما قبلها من الذنوب ما لم تُؤتَ كبيرة، وذلك الدهر كله**» [رواه مسلم]

*"ማንኛውም ሙስሊም የፈርድ (የግዴታ) ሶላት ደርሶበት፤ (የዚያን ሶላት) ዉዱዑን አስተካክሎ፣ ‹ኹሹዑ›ን እና ‹ሩኩዑ›ን አሳምሮ አይሰግድም ለሰራቸው ወንጀሎቹ ማበሻ ቢሆንለት እንጂ ። ትላልቅ ወንጀሎችን ከራቀ ። በእንዲሁ ሁኔታ አመቱን ሙሉ (ወንጀሉ ይታበስለታል) ።"*[2]

10. *ሶላት፡-* ከዕሳት ነፃ መውጫ፤ ከአደጋ መጠበቂያ፤ ከሀያሉ ጌታ (ቁጣ) መዳኛ፤ ከደጋጎች ጋር ጀነትን መጎናጸፊያ ነው ። መልዕክተኛው ﷺ ይህን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፡ -

---

[1] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።
[2] ሙስሊም ዘግቦታል።

«لن يلج النار أحد صلَّى قبل طلوع الشمس وقبل غروبها» يعني الفجر والعصر [رواه مسلم]

*"ማንኛውም ከፀሀይ መግቢያና መውጫ በፊት የሰገደ (ሰው) እሳት አይገባም ::"*[1] ማለትም ሱብሂና አስር ሶላትን

«من صلَّى الصبح فهو في ذمة الله، فانظر يا ابن آدم، لا يطلبنَّك الله من ذمته بشيء» [رواه مسلم]

*"ሱብሂን (በጀምዓ) የሰገደ በአላህ ጥበቃ ስር ነው :: የአደም ልጅ ሆይ አስተውል ! (በሱ ጥበቃ ስር የገባን ሰው በመተናኮስ ) አላህ (በበቀል) አይፈልግህ ::"*[2]

11. ሶላት፡- የድል እና የስኬት መሰረት፤ የስራ ተቀባይነት እና ከእሳት ነጻ የመሆን መረጃ፤ ጧትና ማታ ከሚሰሩ ስራዎች ሁሉ አላህ ባሪያውን በመጀመሪያ የሚተሳሰብበት ተግባር ነው :: ለዚህም የሚከተለው የአላህ ቃል ዋቢ ነው ::

﴿قَدْ أَفْلَحَ ٱلْمُؤْمِنُونَ ۝١ ٱلَّذِينَ هُمْ فِى صَلَاتِهِمْ خَٰشِعُونَ ۝٢﴾ المؤمنون: ١ - ٢

﴿ وَٱلَّذِينَ هُمْ عَلَىٰ صَلَوَٰتِهِمْ يُحَافِظُونَ ۝٩ أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْوَٰرِثُونَ ۝١٠ ٱلَّذِينَ يَرِثُونَ ٱلْفِرْدَوْسَ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ۝١١﴾ المؤمنون: ٩-١١

*"ምዕመናን ፍላጎታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ (ዳኑ):: እነዚያም እነሱ በስግደታቸው ውስጥ (አላህን) ፈሪዎች ::"*[3] ከዚያም አለ፤ *"እነዚያም እነሱ በስግደታቸው ላይ የሚጠባበቁ፤ እነሱ ወራሾች ናቸው፤ እነዚያ ፊርደውስን (ላዕላይ ገነትን ) የሚወርሱ በሷም ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው ::"*[4]

---

[1] ሙስሊም ዘግቦታል::
[2] ሙስሊም ዘግቦታል::
[3] አል-ሙዕሚን፡- 1-2
[4] አል-ሙዕሚን፡- 9-11

ነብዩም ﷺ እንዲህ ብለዋል:-

«**إنما ينصر الله هذه الأُمَّة بضعيفها، بدعوتهم وصلاتهم وإخلاصهم**» [رواه النسائي وصححه الألباني]

*“አላህ ይህንን ህዝብ የሚረዳው በአቅመ ደካሞች ፀሎት፣ ስግደት እና ለአላህ ባላቸው ፍጹምነት (ኢኽላስ) ነው ::”*[1]

«**صلاة في إثر صلاة لا لغو بينهما كتاب في عليين**» [أخرجه أبو داود وحسنه الألباني]

*“በሁለት ሶላቶች መሀል ምንም የማይጠቅሙ (ውዳቂ) ነገሮችን ሳይፈፅም አከታትሎ የሰገደ በኢሊይን (የደጋግ አገልጋዮች ስራ በሚጻፍበት መዝገብ ) ይጻፋል::”*[2]

«**أول ما يُحاسب عليه العبد يوم القيامة الصلاة، فإن صلحت صلح سائر عمله، وإن فسدت فسد سائر عمله**» [أخرجه الطبراني والضياء وصححه الألباني]

*“ማንኛውም ባሪያ የትንሳዔ ቀን (ጌታው ዘንድ ) ከስራዎቹ በመጀመሪያ የሚመረመረው ከሶላቱ ነው :: ሶላቱ የተስተካከለ ከሆነ ቀሪ ስራዎቹም የተስተካከሉ ይሆናሉ :: ሶላቱ የተበላሸ ከሆነ ቀሪ ስራዎቹም የተበላሹ ይሆናሉ ::”*[3]

12. *ሶላት:-* የጉዞ ስንቅ፤ የመንፈስ እርካታ፤ የአካል መርጊያ፤ የአዕምሮ ብርሃንና የልብ ሰላም መጎናጸፊያ ነው :: አላህ እንዲህ ይላል: -

---

[1] ነሳዒ ዘግቦታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።
[2] አቡ ዳዉድ ዘግበውታል። አልባኒ ሀሰን ብለውታል።
[3] ጠበራኒና ደያዕ ዘግበውታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።

﴿مُّحَمَّدٌ رَّسُولُ ٱللَّهِۚ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥٓ أَشِدَّآءُ عَلَى ٱلۡكُفَّارِ رُحَمَآءُ بَيۡنَهُمۡۖ تَرَىٰهُمۡ رُكَّعٗا سُجَّدٗا يَبۡتَغُونَ فَضۡلٗا مِّنَ ٱللَّهِ وَرِضۡوَٰنٗاۖ سِيمَاهُمۡ فِي وُجُوهِهِم مِّنۡ أَثَرِ ٱلسُّجُودِۚ﴾ الفتح: ٢٩

*«ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ። ከርሱ ጋር ያሉት (ባልደረቦቹ) በከሀዲ ላይ ብርቱ ሲሆኑ፤ እርስ በእርሳቸው ይተዛዘናሉ ። ከአላህ ቱርፋትንና ውዴታን የሚፈልጉ ሲሆኑ አጎንባሾች እና ሰጋጆች ሆነው ታያቸዋለህ ። ምልክታቸው በፊቶቻቸው ላይ የሚታይ የስግደታቸው ፈለግ ሲሆን ።»*[1]

﴿وَلَقَدۡ نَعۡلَمُ أَنَّكَ يَضِيقُ صَدۡرُكَ بِمَا يَقُولُونَ ٩٧﴾ الحجر: ٩٧

*«አንተም በሚሉት ነገር ልብህ የሚጠብ መኾኑን በእርግጥ እናውቃለን።»*[2]

**መልዕክተኛውም ﷺ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቦዋል፡ -**

«**يا بلال! أقم الصلاة، أرحنا بها**» [رواه أحمد وأبو داود وصححه الألباني]

**"ቢላል ሆይ ቁም! (ኢቃም በልና) በሶላት እረፍትን ስጠን ።"**[3]

**"ሶላት ብርሃን ነው ።"**[4] «**الصلاة نور**» [رواه مسلم]

«**من حافظ على الصلاة كانت له نورًا وبرهانًا ونجاة يوم القيامة، ومن لم يحافظ علي الصلاة لم يكن له نور ولا برهان ولا نجاة يوم**

---

[1] አል-ፈትህ፡- 29
[2] ሂጅር 97
[3] አህመድና አቡዳውዘግበውታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።
[4] ሙስሊም ዘግቦታል።

القيامة، وكان يوم القيامة مع قارون وفرعون وهامان وأُبِّي بن خلف» [رواه أحمد بإسناد جيد كما قال المنذري]

*"ሶላትን ተጠባብቆ (ጊዜውን ጠብቆና በተሟላ ስርዓት ) የሰገደ እንደሆነ የትንሳዔ ቀን ብርሃን፣ መረጃ እና ከቅጣት ነጻ መውጫ ይሆንለታል :: ስርዓቱን አሟልቶ ያልሰገደ እንደሆነ የትንሳዔ ቀን ብርሀንም፣ መረጃም፣ ከቅጣት መዳኛም የለውም :: ከነቃሩን፣ ፊርዐውን፣ ሃማን እና ኡበይ ብን ኸለፍ ጋር ይሆናል ::"*[1]

13. *ሶላት:-* ሰይጣንን ማስቆጪያ፤ ከሀዲያንን እና አመጸኞችን ማናደጃ ነው:: አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّمَا يُرِيدُ ٱلشَّيْطَٰنُ أَن يُوقِعَ بَيْنَكُمُ ٱلْعَدَٰوَةَ وَٱلْبَغْضَآءَ فِى ٱلْخَمْرِ وَٱلْمَيْسِرِ وَيَصُدَّكُمْ عَن ذِكْرِ ٱللَّهِ وَعَنِ ٱلصَّلَوٰةِ ۖ فَهَلْ أَنتُم مُّنتَهُونَ ﴾ المائدة: ٩١

*"ሰይጣን የሚፈልገው በሚያሰክር መጠጥና በቁማር በመካከላችሁ ጠብ እና ጥላቻ እንዲሰፍን ነው :: እንዲሁም ከውዳሴና እና ከሶላት ይከለክላችኋል :: (ከዚህ ድርጊት ) አትቆጠቡምን ?!"* [2]

*መልዕክተኛውም ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-*

"«إذا قرأ ابن آدم السجدة فسجد، اعتزل الشيطان يبكي يقول: يا ويلي! أُمر ابن آدم بالسجود فسجد فله الجنة، وأُمرت بالسجود فأبيت فلي النار» [رواه مسلم]

*"የአደም ልጅ (ቁርዓንን) ቀርቶ ሱጁድ[3] ባደረገ ጊዜ ሰይጣን እያለቀሰ ከሱ ይሸሻል :: ይላልም ዋ ጥፋቴ ! የአደም ልጅ ሱጁድ እንዲያደርግ ታዘዘ፤ ሰገደም :: ለሱ ጀነት*

[1] አህመድ ዘግቦታል፡፡ሙንዚሪ ሰነዱ ጠንካራ ነው ብለዋል፡፡
[2] አል-ማኢዳ፡- 91
[3] ሱጁዱ ቲላዋ ያለባቸውን የቁርዓን አንቀጽ

*አለለት። ስጁድ እንዳደርግ ታዘዝኩ፤ እንቢተኛም ሆንኩ ። ለእኔ እሳት አለልኝ ።"*[1]

«**ما حسدَتْكم اليهود على شيء ما حسدَتْكم على السلام والتأمين**» [أخرجه أحمد وصححه الألباني]

*"አይሁዳውያን በሰላምታችሁ እና (በሶላት ላይ ሆናችሁ ) ኣሚን -ጌታችን ተቀበለን - በማለታችሁ እንደሚመቀኟችሁ በምንም ነገር አይመቀኟችሁም ።"*[2]

*14. ሶላት፡- የምስጋና እና አድናቆትን መግለጫ፤ የላቀ የሆነውን ጌታ ማወደሻ፤ የሱብሃነላህ፣ የአልሀምዱሊላህ እና የላኢላሀ-ኢለሏህ*[3] ክምችት ነው ።

ሙጊራ ብን ሺዓብ (አላህ ይውደድለትና ) ባስተላለፈው ሀዲስ እንዲህ ብሏል፡ -

أقام النبي حتى تورَّمت قدماه. فقيل له: قد غفر الله لك ما تقدم من ذنبك وما تأخر؟ فقال: «**أفلا أكون عبدًا شكورًا**» [متفق عليه]

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ተረከዛቸው እስኪሰነጣጠቅ (ሶላትን በመስገድ ) ይቆሙ ነበር ። አላህ ያለፈውንም ሆነ የበፊቱን ወንጀል ምሮሎት ሲያበቃ (እንዴት ይህን ያህል ይደክማሉ )? በማለት ተጠየቁ ። አሉም፡- *"አመስጋኝ ባሪያ (አገልጋይ ) አልሆንምን ?!"*[4]

«**يصبح على كلِّ سُلامى من أحدكم صدقة، فكلُّ تسبيحة صدقة، وكلُّ تحميدة صدقة، وكلُّ تهليلة صدقة، وكلُّ تكبيرة صدقة، وأمر بالمعروف صدقة، ونهي عن المنكر صدقة، ويجزئ من ذلك ركعتان يركعهما من الضحى**» [رواه مسلم]

*"እያንዳንዳችሁ በየዕለቱ በአካል መገጣጠሚያ ቁጥር ልክ ሰደቃ (ምጽዋት) ይጠበቅባችኋል ። እያንዳንዱ ሱብሃነላህ፣ አልሀምዱሊላህ፣ ላኢላሃ-ኢለሏህ፣ በጥሩ*

---

[1] ሙስሊም ዘግቦታል።
[2] አህመድ ዘግቦታል።አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።
[3] *ሱብሃነላሁ-* ለአላህ ጥራት ይገባው። *አልሀምዱ ሊላሁ-* ምስጋና ለአላህ ይገባው። *ላኢላሀ-ኢለሏህ፡-* ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም።
[4] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

*ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል ሰደቃ ናቸው ። በረፋድ የሚሰገድ ሁለት ረከዓ ሶላት (ሶላቱ ዱሃ) ይህን ሁሉ ያብቃቃዋል ።"*[1]

15. *ሶላት፡-* ከስሜታዊነት መዳኛ፤ ከክፉና ጸያፍ ተግባራት መከልከያ፤ ጭንቀትንና በሽታን ማባረሪያ ነው ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ تَنۡهَىٰ عَنِ ٱلۡفَحۡشَآءِ وَٱلۡمُنكَرِۗ﴾ العنكبوت: ٤٥

*"ሶላት ከመጥፎና ከአጸያፊ ተግባራት ትከላከላለች ።"*[2]

ነቢዩም ﷺ ይህን ሲያጠናክሩ፡-

**«عليكم بقيام الليل، فإنه دأب الصالحين قبلكم، وقربة إلى الله تعالى، ومنهاة عن الإثم، وتكفير للسيئات، ومطردة للدَّاء عن الجسد»** [أخرجه أحمد والترمذي وصححه الألباني].

*"የሌሊት ሶላትን አደራ ። ከእናንተ በስተፊት የነበሩ ደጋጎች የዘውትር ተግባር ነውና ። በሌሊት መስገድ፡ - ወደ ላቀው አላህ መቃረቢያ፤ ከወንጀል መጠበቂያ፤ ከመጥፎ ተግባራት መጽጃ እና በሽታን ከአካል ማባረሪያ ነው ።"*[3]

## አንተ ሶላትን የተዉክ ሆይ!!

*አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ ! ሶላትን ትተህ* ከእስልምና ምን ቀረህ ? ሶላት የኢስላም ምሰሶ ፤ የ *ኢማን መገለጫ* -ካባ- *መሆኑን አታውቅምን* !?

*አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ !* አንተ ስትቀር ሁሉም ፍጥረታት ለጌታቸው ሰጋጆች ናቸው፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡ -

---

[1] ሙስሊም ዘግቦታል፡፡
[2] አል-አንከቡት፡-45
[3] አህመድና ቱርሚዚይ ዘግበውታል፡፡ አልባኒ ሶሂህ ብለውታል፡፡

﴿أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَسۡجُدُۤ لَهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ وَٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُ وَٱلنُّجُومُ وَٱلۡجِبَالُ وَٱلشَّجَرُ وَٱلدَّوَآبُّ وَكَثِيرٞ مِّنَ ٱلنَّاسِۖ وَكَثِيرٌ حَقَّ عَلَيۡهِ ٱلۡعَذَابُۗ﴾ الحج: ١٨

*"በሰማያት ያለው ሁሉ፤ በምድርም ያለው ሁሉ፤ ፀሀይና፣ ጨረቃም፣ ከዋክብትም፣ ተራሮችም፣ ዛፎችም፣ ተንቀሳቃሶችም፣ ከሰዎች ብዙዎችም ለአላህ የሚሰግዱ መሆናቸውን አታውቅምን !? ብዙዎችም ቅጣት ተገባቸው :: አላህ የሚያዋርደው ሰው ለርሱ ምንም አክባሪ የለውም፤ አላህ የሻውን ይሰራልና ::"*[1] **አንተም የማትሰግድ ከሆነ ከነዚያ ቅጣት ከተወሰነባቸው አንዱ ትሆነናለህ ::**

**አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ ! ሶላትን መተው ክህደትና (በአላህ ላይ ) ማጋራት መሆኑን አታውቅምን !? ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡ -**

«**بين الرجل وبين الشرك والكفر ترك الصلاة**» [رواه مسلم]

*«በሰውየውና በሽርክ ወይም በክህደት መሀል (ያለው) ሶላትን መተው ነው ::"*[2]

«**العهد الذي بيننا وبينهم الصلاة: فمن تركها فقد كفر**» [أخرجه أحمد والترمذي وصححه الألباني].

*"በኛና በነሱ (በካህዲያን) መሀል ያለው ቃል -ኪዳን (ድንበር) ሶላትን መተው ነው :: (ሶላትን) የተወ በእርግጥ ካደ ::"*[3]

**አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ ! ሶላትን መተው እንዲሁም (ከሶላት) መዘናጋት ሙናፊቅነት መሆኑን አታውቅም !?**

---

1 አል-ሀጅ፡ 18
2 ሙስሊም ዘግቦታል።
3 አህመድና ቲርሚዚይ ዘግበውታል።

**አላህ እንዲህ ብሏል ፦**

﴿إِنَّ ٱلۡمُنَٰفِقِينَ يُخَٰدِعُونَ ٱللَّهَ وَهُوَ خَٰدِعُهُمۡ وَإِذَا قَامُوٓاْ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ قَامُواْ كُسَالَىٰ يُرَآءُونَ ٱلنَّاسَ وَلَا يَذۡكُرُونَ ٱللَّهَ إِلَّا قَلِيلٗا ١٤٢﴾ النساء: ١٤٢

***"ሙናፊቆች አላህን ሊያታልሉ ይፈልጋሉ፤ እሱ አታላያቸው ሲሆን :: ወደ ሶላት ሲቆሙ እየሰለቹ፣ ለሰዎች የሚያሳዩ ሆነው ይቆማሉ :: አላህንም ጥቂትን እንጂ አያወሱም ::"***[1]

**ነቢዩም ﷺ ይህን ማስተላለፋቸው ተዘግቧል ::**

«**أثقل الصلاة على المنافقين صلاة العشاء وصلاة الفجر، ولو يعلمون ما فيهما لأتوهما ولو حبوًا**» [متفق عليه].

***"በሙናፊቆች ላይ እጅግ የሚከብደው ሶላት ኢሻዕ እና ሱብሂ ነው :: (ሁለቱን በመስገድ) የሚገኘውን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ እየዳሁም ቢሆን (ወደ መስጊድ) ይመጡ ነበር ::"***[2]

***አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ !*** **እስቲ አስተንትን ሙናፊቆች ለይዩልኝ (ሪያዕ) ቢሆንም እንኳ ይሰግዳሉ፤ አንተ ግን በፍጹም አትሰግድም !!**

***አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ፦*** **- ሶላትን መተው ዝንጉነት እና የልብ መድረቅ መሆኑን አታውቅምን !? ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡ -**

«**لينتهين أقوام عن ودعهم الجمعات، أو ليختمن الله على قلوبهم، ثم ليكونن من الغافلين**» [رواه مسلم].

***"ህዝቦች የጁምዓ ሶላትን ከመተው ይከልከሉ ! ወይም አላህ በልቦቻቸው ላይ ያሽግባቸዋል :: ከዚያም ከዝንጉዎች ይሆናሉ ::"***[3]

---

[1] ኒሳዕ፡- 142

[2] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

[3] ሙስሊም ዘግቦታል።

*አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ፡ - ሶላትን መተው ስራን ሁሉ እንደሚያበላሽ* **አልሰማሐሃምን !? የሚከተለውን የነቢዩን ﷺ ንግግር ተመልከት ::**

«**من ترك صلاة العصر حبط عمله**» [رواه البخاري].

*"የአስርን ሶላት የተወ ስራው በርግጥ ተበላሸበት ::"*[1]

*አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ ! ሶላትን መተው ከከሀዲያንና ወንጀለኞች ጋር ለእሳት ቅጣት እንደሚዳርግ አታውቅምን !?*

**የጀነት ሰዎች የጀሀነም ሰዎችን (ጀሀነም የገቡበትን ምክንያት ) ሲጠይቋቸው የሚሰጧቸውን ምላሽ ሲናገር አላህ እንዲህ ይላል፡ -**

﴿مَا سَلَكَكُمْ فِي سَقَرَ ۝٤٢ قَالُوا لَمْ نَكُ مِنَ الْمُصَلِّينَ ۝٤٣﴾ المدثر: ٤٢ - ٤٣

**"ሰቀር (የገሀነም ጉድጓድ ) ውስጥ ምን አስገባችሁ ? (እነሱም) ይላሉ፡- ከሰጋጆች አልነበርንም... ::"**[2]

**እንዲሁም በሌላ ምዕራፍ፡ -**

﴿فَخَلَفَ مِنْ بَعْدِهِمْ خَلْفٌ أَضَاعُوا الصَّلَاةَ وَاتَّبَعُوا الشَّهَوَاتِ فَسَوْفَ يَلْقَوْنَ غَيًّا ۝٥٩﴾ مريم: ٥٩

*"ከነሱም በኋላ ሶላትን ያጓደሉ፣ ስሜታቸውንም የተከተሉ ምትኮች ተተኩ :: ለወደፊት ገይን (የገሀነም ሸለቆ ) ይገባሉ ::"*[3]

---

[1] ቡኻሪ ዘግቦታል::

[2] ሙደሲር፡- 42-43

[3] መርየም፡- 59

**አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ ! ሶላትን በመተውህ ከባድ መዓት (ጥፋት) ያረፈብህ መሆኑን አታውቅምን !?**

**ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡ -**

«**الذي تفوته صلاة العصر، فكأنما وتر أهله وماله**» [رواه البخاري]

***"የአስር ሶላት ያመለጠው ቤተሰቦቹንና ንብረቱን እንደ አጣ (እንደ ተነጠቀ) ነው፡፡"[1]***

**የአምስቱንም ወቅት ሶላት መተውህስ ምን ያስከትል ይሆን !?**

***አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ ! ሶላትን መተው መረበሽን፣ አለመረጋጋትን፣ ጭንቀትን፤ የኑሮ ጥበትን (እንደሚያመጣ) አታውቅምን !?***

**አላህ እንዲህ ይላል፡ -**

﴿ وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِى فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ أَعْمَىٰ ﴿١٢٤﴾ قَالَ رَبِّ لِمَ حَشَرْتَنِىٓ أَعْمَىٰ وَقَدْ كُنتُ بَصِيرًا ﴿١٢٥﴾ قَالَ كَذَٰلِكَ أَتَتْكَ ءَايَـٰتُنَا فَنَسِيتَهَا ۖ وَكَذَٰلِكَ ٱلْيَوْمَ تُنسَىٰ ﴿١٢٦﴾ ﴾ طه: ١٢٤ - ١٢٦

*«ከግሳጼዬ የዞረ፤ የጥበት ህይወት አለለት፤ የትንሳኤም ቀን እውር ሆኖ እንቀሰቅሰዋለን ፡፡ ጌታዬ ሆይ ለምን እውር አድርገህ ቀሰቀስከኝ ? በርግጥ አይናማ የነበርኩ ስሆን ይላል ፡፡ (ነገሩ) እንደዚሁ ነው ፡፡ ተዓምራችን መጥቶልህ ሳለ እንደዘነጋኸው አንተም ዛሬ ትዘነጋለህ ይለዋል ፡፡»[2]*

***ዋ ንዴትህ ! ዋ ፀፀትህ ! አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ ፡፡ እንዴት ጊዜ ያልፉል፤ እድሜህ***

---

[1] ቡኻሪ ዘግበታል፡፡
[2] *ጣሃ፡-* 124-126

(ያለ አግባብ) ይገባደዳል; ልብህ ከጌታህ ተጋርዶ ሳለ !? እንዴትስ በቅርቢቱ አለም (ዱንያ) ከሚገኙት ነገሮች ሁሉ ይበልጥ ጣፋጭ እና ማራኪ የሆነውን ነገር ሳትቀምስ ዱንያ ን ትሰናበታታለህ!? ይህም አላህን በማምለክ፣ በማውሳት፣ በማመስገን እና ለርሱም በመስገድ የሚገኝ ሲሆን ::

*አንተ ሶላትን የተውክ ሆይ ! ለሶላትህ ቀላል ስፍራ የሰጠኸው አንተ ዘንድ ታላቅ ስፍራ የሚሰጠው ምን ይሆን ? ሶላቱን ያጓደ ሌሎች ስራዎቹን ይበልጥ እንደሚያጓድል አታውቅምን!?*

*ሀሰን እንዲህ ብሏል: - "የአደም ልጅ ሆይ ! ሶላትህ አንተ ዘንድ ጥሩ ስፍራ ከሌለው ምንድን ነው አንተ ዘንድ ጥሩ ስፍራ ሊኖረው የሚችለው !?"*

*አንተ ዝንጉ የሆንክ ሆይ ! ወደ ጌታህ ተመለስ ! ሶላትህን ትተህ ሞት ከመምጣቱ በፊት ::*

**አንተ ሶላትን ቸላ የምትል ሆ!ይ**

- የታላቁን ሶላት ደረጃ ካወቅክ
- የሰጋጆችን ቁጥር ስፍር የሌለውን ሽልማት መመልከት ከቻልክ (እና)
- ሶላትን የሚያጓድሉ ሰዎችን ብርቱ ቅጣት ከተገነዘብክ በኋላ

**አሁንስ ምላሽህ ምን ይሆ?ን**

- ሶላትን በማጓደልና ቸላ በማለት ትቀጥላለህን !?
- ሶላትን ትቶ መተኛትንና ከወቅቱ ማዘግየትን ትገፋበታለህን !?

*ወንድሜ ሆይ !*

- ❷ የት አለ ከፍ ያለው ሞራልህ ?
- ❷ የት አለ ጠንካራው ቁርጠኝነትህ ?

- ❷ የቱ ላይ ነው ለጀነት ታጥቆ መነሳት ?
- ❷ የት አለ የሶላትን ወቅት መጠባበቅ ?
- ❷ (ኸረ) የት አለ ወደ ጁምዓ እና ወደ ጀምዓ ሶላት በጊዜ መሄድ ?

## ሰዎች ከሶላት አንጻር ያላቸው ደረጃ

ኢማም ኢብነል ቀዩም (አላህ ይዘንላቸው ) እንዲህ ብለዋል፡ - “ሰዎች ከሶላት አንጻር በአምስት ደረጃዎች ይከፈላሉ ።”

**አንደኛው-** የሶላትን ዉዱዕ፣ ጊዜያት፣ ህግጋቱን እና ማዕዘኑን በማጓደል ራሱን የበደለ ነው።

**ሁለተኛው፥** (የሶላቱን) ጊዜውን፣ ህግጋቱንና ግልጽ የሆኑ ማዕዘኖቹን እና ውዱዑን የጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ነፍሱን በሶላቱ ውስጥ ከሚመጡበት የተለያዩ ሀሳቦች (ውስወሳዎች) ለመታደግ ትግል ያላደረገ እና ከሀሳቡ ጋር የነጎደ ነው ።

**ሶስተኛው-** ህግጋቱንና ማዕዘኑን የጠበቀ እና ከተለያዩ በሶላት ውስጥ ከሚመጡበት ሀሳቦች ጋር ትግል የገጠመ ነው ። እንዲህ አይነቱ ሰው ሶላቱን በመስገድ እና (ሶላቱ) እንዳይሰረቅበት ከጠላቱ (ሰይጣን) ጋር ግብግብ የገጠመ ነው ። ይህ ሰው በሶላትና በጂሃድ (በትግል) ላይ ነው።

**አራተኛ፥** ለመስገድ ሲነሳ የሶላቱን ሙሉ ስርዓት፣ ማዕዘኖቹን እና ህግጋቱን አሟልቶና ጠብቆ ይሰግዳል ። ሶላቱ ምንም እንዳይጓደልበት ደንቡንና ስርዓቱን በመጠበቅ ላይ ሰጥሟል። ጭንቀቱ ሁሉ ሶላቱን በተገቢ ሁኔታ አሟልቶ ለመፈጸም ነው ። ከዚህ ባሻገር ልቡ በሶላቱ እና ጌታውን በማምለክ ላይ ተመስጧል ።

**አምስተኛው-** አሰጋገዱ አራተኛው ላይ እንደተገለጸው ሆኖ ከዚህም በተጨጫሪ ልቡን ይዞ እጌታው ዘንድ ያኖራታል ። በልቡ ጌታውን እንደሚመለከት እያሰበ፤ እርሱን

እየተጠባበቀ፤ በጌታው ውዴታና ታላቅነት በመሞላት፤ እሱ ዘንድ እንዳለና እንደሚያየው ሆኖ (ይሰግዳል):: ከእንደዚህ አይነት ሰው እነዚያ (ተመላላሽ የሆኑት) ሀሳቦች ሁሉ ተወግደዋል :: በርሱና በጌታው መሀል ምንም አይነት ግርዶሽ የለም:: የእንደዚህ አይነት ሰው ሶላት ከሌላው ሰው (ሶላት) ጋር ሲነጻጸር በሰማይና በምድር መሀል ካለው ልዩነት የላቀና የገዘፈ ነው :: ይህ ሰው በሶላቱ ውስጥ (ታላቅ በሆነው) ጌታው ተጠምዷል :: ጌታዉንም የአይኑ ማረፊያ አድርጓል ::

**<u>ምንዳቸው</u>**

- አንደኛው፡- ይቀጣል::
- ሁለተኛው፡- ይመረመራል ::
- ሶስተኛው፡- ወንጀሉ ይሰረዝለታል ::
- አራተኛው፡- ይመነዳል::
- አምስተኛው፡- ጌታው ወደ እርሱ የቀረበ ይሆናል :: ሶላቱን የአይኑ ማረፊያ በማድረጉ (ታላቅ) ድርሻ አለው ::

በቅርቢቱ አለም ሶላቱን የዐይኑ ማረፊያ ያደረገ፤ በትንሳዔው እለት ጌታው የዐይኑ ማረፊያው ይሆናል :: በቅርቢቱ ዓለምም ቢሆን ዐይኑ በጌታው ትረካለች :: አላህን የዐይኑ ማረፊያ ያደረገ የሁሉም ዐይን ማረፊያ ይሆናል :: አላህን የዐይኑ ማረፊያ ያላደረገ ግን የዚህች አለም (ዱንያ) አፍቃሪ ሆኖ (በመጨረሻም) ከፀፀተኞች ይሆናል ::

*ውድ ወንድሜ ሆይ ! ይህ ሰዎች በሶላት አሰጋገዳቸው የሚኖራቸው ደረጃ ነው :: አንተ በየትኛው ደረጃ ላይ ነው ያለኸው ? ራስህን ገምግም ! በሶላትህ ሚዛን መዝናት፤ የሶላት ሚዛን አይሳሳትምና !!*

*ወንድሜ ሆይ ! መጨረሻህ ብስባሽ ሆኖ ሳለ፤ ይህ ሁሉ መዘናጋት ለምንድን ነው ? ዛሬ*

ነገ ማለቱ አልበዛም ? ጉድለትህ በርግጥ ከልክ በላይ ሆኗል ። እድሜህ ያለቀ መሆኑን (አስጠንቃቂ) አላስጠነቀቀህም? (ለመጪው ዓለም ) አትዘጋጅምን? በርግጥ ስራህ ከፍቷል።

*ወንድሜ ሆይ!* ስንትና ስንት ጊዜ ነው ‹‹ *ሙዓዚኑ*›› (አዛን አድራጊው) ወደ ሶላት የጠራህ አንተ ተኝተህ ሳለህ ? ወደ መስጊድ በመጣህም ጊዜ አካልህን ብቻ ይዘህ ልብህን ረስተህ ነው! (ነፍስያህም) በርግጥ (በትክክል) ሰግደሃል ትለሃለች ተቆጣጣሪ እንዲኖርብህ አትሻምና።

## የሶላትን ልቅና የምናጎላበት መንገዶች

ሶላትን አሳምረን እንድንሰግድ እና ክብሩን እንድናልቅ የሚረዱን ብዙ መንገዶች አሉ ።

1ኛ ፡- ህግጋቱንና ጊዜውን ጠብቆ መስገድ ።

2ኛ፡- ማዕዘናቶቹ እና ግዴታዎቹ ሙሉ በሙሉ መተግበራቸውን መፈተሽ ።

3ኛ፡- ዋጂብ ሶላቶችን ለመስገድ (ወደ መስጊድ) መጣደፍ ።

4ኛ፡- ከሶላት ህግጋቶችና ደንቦች አንዷ እንኳ ስትጓደል በማዘን፣ በመናደድ እና በመፀፀት ሌላ ጊዜ ላለመድገም መጣር ።

ለምሳሌ፡-

- ብቻውን የሰገደ ሰው፡- ሶላቱ ተቀባይነት ቢያገኝ እንኳ 27 ደረጃ እንዳመለጠው በመገንዘብ - የጀምዓ ሶላት ስላመለጠው ማዘን ።
- የአላህ ውዴታን የሚያስገኘውን የጀመሪያው የሶላት ወቅት ስላለፈው መቆጨት።
- ምንዳውን ቢያውቁ ኖሮ እጣ እንኳን በመጣጣል ለማግኘት በታገሉ ነበር የተባለለትን የመጀመሪያው የሶላት ሰልፍ (ሶፍ) ባለማግኘቱ መናደድ ።

★ በሶላቱ ውስጥ ሀሳቡን ባለመቆጣጠሩና ለአላህ ባለመተናነሱ (ኹሹዕ ባለማድረጉ ) መፀፀት:: (ኹሹዕ) የሶላት ህይወት መዝሪያ እስትንፋስ መሆኑንና ሶላት ያለ እሱ ህይወት እንደሌለው (የሞተ) ሰው አካል እንደሆነ በመገንዘብ :: ነቢዩም ﷺ ይህን ማለታቸው ተዘግቧ: -

«إن العبد ليُصلِّي الصلاة وما كتب له إلا عشرها، تسعها، ثمنها، سبعها، سدسها، خمسها، ربعها، ثلثها، نصفها» [رواه أحمد وأبو داود وحسنه الألباني].

*"አንድ የአላህ ባሪያ ሰላቱን ይሰግዳል :: (ነገር ግን ደንቡንና ህግጋቱን ባለሟሟላቱ ) ከስግደቱ (ምንዳ) አንድ አስረኛ፤ ወይም አንድ ዘጠነኛ፣ ወይም አንድ ስምንተኛ፣ ....፣ ወይም አንድ ሁለተኛ እንጂ አይመዘገብለት ::"*[1]

«إذا قمت في صلاتك؛ فصلِّ صلاة مودِّع» [رواه أحمد وابن ماجة وصححه الألباني]

*"ሶላትን ልትሰግድ ስታስብ፤ የመሰነባበቻ ሶላትን ስገድ ::"*[2]

## ተቀባይነት ያለው ሶላት

*ውድ ወንድሜ ሆይ ! የሚከተሉት ነጥቦች ሶላትህን ተጠባብቀህ በተደነገገው መሰረት እንድትሰግድ እና በሶላትህም ተጠቃሚ እንድትሆን ይረዱሃልና አጥብቀህ ያዛቸው ::*

1. **ለሶላትህ ውዱዕን አሳምር**

**ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋልና: -**

---

[1] አህመድና አቡ ዳዉድዘግበውታል። አልባኒ ሀሰን ብለውታል።
[2] አህመድና ኢብን ማጃህ ዘግበውታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።

«ما من مسلم يتوضأ فيُحسن وضوءه، ثم يقوم فيُصلي ركعتين، يُقبل عليهما بقلبه ووجهه إلا وجبت له الجنة» [رواه مسلم]

*"አንድ ሙስሊም ውዱዑን አሟልቶ ፤ ከዚያም በልቡም ሆነ በፊቱ ወደ አላህ ተመልሶ ሁለት ረከዓ አይሰግደም ። ለሱ ጀነት የተወሰነች ብትሆን እንጂ ።"*[1]

2. **ከቤትህ ውዱዕ አድርገህ ውጣ**

**ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡ -**

«من خرج من بيته مُتطهِّرًا إلى صلاة مكتوبة فأجره كأجر الحاجِّ المُحرم» [رواه أحمد وأبو داود وحسنه الألباني]

**"ፈርድ ሶላትን ለመስገድ ውዱዕን አድርጎ ወደ መስጊድ የሄደ ምንዳው፡- ሀጅ እያደረገ ካለ ሰው ጋር እኩል ።"**[2]

3. **ሶላትን በመጀመሪያው ወቅት ለመስገድ ተጣባበቅ**

**ነቢዩ ﷺ ይህን ተናግረዋልና፡ -**

«صلاة الجماعة أفضل من صلاة الفذ بسبع وعشرين درجة» [متفق عليه].

*"ከስራዎች ሁሉ በላጩ፤ ሶላትን በጊዜው መስገድ ነው ።"*[3]

4. **ሶላትን በጀምዓ መስገድ የዘውትር ተግባርህ ይሁን**

**ይህን ሀዲስ በተግባር ለመለወጥ፡ -**

«صلاة الجماعة أفضل من صلاة الفذ بسبع وعشرين درجة» [متفق عليه].

*"በጀምዓ መስገድ ለብቻ ከመስገድ በሀያ ሰባት ደረጃ ይበልጣል ።"*[4]

---

[1] ሙስሊም ዘግቦታል።
[2] አህመድ እና አቡዳዉድ ዘግበውታል።" አልባኒ ሀሰን ብለውታል።
[3] ቡኻሪ እና ሙስሊም ዘግበውታል።

5. *ተክቢረተል ኢህራምን ለማግኘት ጥረት አድርግ*

**ነቢዩ ﷺ እንደሚከለው ብለዋልና፡ -**

«**أن من صلى لله أربعين يومًا في جماعة يدرك التكبيرة الأولى، كُتب له براءتان: براءة من النار وبراءة من النفاق**» [رواه أحمد وصححه الألباني]

*"አርባ ቀን በተከታታይ የመጀመሪያው ተክቢራ ሳያመልጠው ለአላህ ብሎ በጀምዓ የሰገደ ከሁለት ነገሮች ነጻ መሆኑ ይጻፍለታል :: ከእሳት ነጻ መሆኑን እና ከንፍቅና ነጻ መሆኑን::"* [2]

6. ወደ መስጂድ መመላለስን አብዛ

**የመልክተኛውን ﷺ ብስራት ታገኛለህና ::**

«**بشر المشائين في الظلم إلى المساجد بالنور التام يوم القيامة**» [رواه أبو داود والترمذي وصححه الألباني]

*"በጨለማ ወደ መስጂድ ተመላላሽ የሆኑ ሰዎችን በትንሳዔው ቀን ሙሉ በሆነ ብርሃን አብስሯቸው ::"* [3]

7. በሶላትህ ሳለህ (ሙሉ) ልብህን አስገኝ

ኢብንቀዩም እንዲህ ብሏል ::"አንድ ባርያ ልቡ ከሶላት እንዳይርቅ የሚያደርገው፡ - ስሜቱ እና ፍላጎቱ ሲመጡበት ልቡን ወደ ጌታው በመመለስ -ከጌታው ጋር ስላለው ግኑኝነት- ራሱን ውጥረት ውስጥ ሲከት ነው :: ይህ ካልሆነ ስሜቱ ልቡን ታሸንፈዋለች፤ ፍላጎቱ

---

[1] ቡኻሪ እና ሙስሊም ዘግበውታል።
[2] አህመድ ዘግቦታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።
[3] አቡዳውድ እና ቲርሚዚይ ዘግበውታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።

ይማርከዋል ። በዚህን ጊዜ ሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ ያገኛል ። ለመወስወስና ሀሳብን ለማብዛት አመቺ ጊዜም ይሆንለታል ።"

8. ልብህን በአላህ ቤቶች ላይ አንጠልጥል፤ ወደ መስጊድ እርምጃን አብዛ

ሶላትን ከሰገድክ በኋላ የሚቀጥለውን ሶላት ተጠባበቅ ። መልዕክተኛው ﷺ አላህ የሱ ጥላ እንጂ ሌላ በሌለበት ቀን ከሚያጠልላቸው ከሰባት አይነት ሰዎች ውስጥ አንዱ እንደሆንክ ናግሯልና ። በተጨማሪም ﷺ እንዲህ ብለዋል፡ -

«ألا أدلكم على ما يمحو الله به الخطايا ويرفع به الدرجات: إسباغ الوضوء على المكاره، وكثرة الخُطى إلى المساجد، وانتظار الصلاة بعد الصلاة، فذلكم الرباط، فذلكم الرباط، فذلكم الرباط» [رواه مسلم].

*"ወደ ወንጀላችሁን የሚያሰርዝላችሁና ደረጃችሁን ከፍ የሚያስደርግላችሁ ተግባር ላመላክታችሁን ?! በአስቸጋሪ ሰዓት ዉዱዕን አሟልቶ ማድረግ፤ ወደ መስጊድ እርምጃን ማብዛት፤ ከሶላት በኋላ ሶላትን መጠባበቅ ። ይህ በአላህ መንገድ ላይ ትግል ነው (3 ጊዜ)።"*[1]

9. የሶላት አህካሞችን (ህግጋቶችን) መማር

የነቢዩን ﷺ የአሰጋገድ ስርዓት እንዴት እንደነበረ ለማወቅ ጣር ። በዚህ ላይ ጠቃሚ የሆኑትን መጽሐፍት (ለምሳሌ ‹‹የነቢዩ ስግደት -ከተክቢር እስከ ተስሊም›› የሚለውን የሸይኽ አልባኒ መጽሀፍን) እና ፓምፕሌቶችን አንብብ ።

10. ከፈርድ ሶላቶች በፊትና በኋላ በሚሰገዱት ሱና ሶላቶችን አጥብቀህ ያዝ

በቤትህ ውስጥ እነዚህን ሶላቶች በመስገድ ላይ ጠንክር ። መልዕክተኛው ﷺ ሱና ሶላትን

---

[1] ሙስሊም ዘግቦታል።

በቤት ውስጥ መስገድ በላጭ መሆኑን አስተምረዋልና ::

«فضل صلاة الرجل في بيته على صلاته حيث يراه الناس كفضل المكتوبة على النافلة» [رواه الطبراني وحسنه الألباني].

*“(ሱና ሶላትን ) ሰዎች ከሚያዩት ቦታ ሆኖ ከሚሰግድ፤ በቤት ውስጥ መስገዱ ይበልጥለታል :: ፈርድ ሶላት ከሱና ሶላት እንደሚበልጠው ያህል ::»*[1]

11. አምሽቶ ከመተኛት ራቅ

ይህም የሱብሂ ሶላትን በእንቅልፍ እንዳታሳልፈው ይረዳሃልና ::

12.መብላት፣ መጠጣት፣ መተኛት፣ መሳቅና ከማይጠቅሙ ሰዎች ጋር መቀላቀልን ከማብዛት ተጠንቀቅ !

እነዚህ እና መሰል ድርጊቶች ሶላት እንዲከብዱህ ምክንያት ይሆናሉና ::

13. ለሱብሂ ሶላት የሚያነቃህን ነገር ተጠቀም

በስልክ፣ በደወል ወይም በተቀጠረ ሰዓት እና በመሳሰሉት በመታገዝ የሱብሂ ሶላት እንዳያልፍህ ጥረት አድርግ ::

14. የሱብሂ ሶላትን በአንድ መስጊድ ላይ አዘውትር

በቀረህ ጊዜ የመስጊዱ የዘውትር ሰጋጆች ይፈልጉሃልና ::

15. በምትቀራው የቁርዓን አንቀጽ መልዕክት አስተንትን

ኢማሙ በሚቀራው የቁርዓን አንቀጽ ወይም የምትቀራቸውን የቁርዓን አንቀጾች በማስተንተን መልእክቱን ለመረዳት ሞክር :: ልብህን ከአንቀሱ ትርጉም ጋር አስኪደው ::

16. ቀደምት ሰለፎች (አበዎች) ለሶላት የነበራቸውን ታላቅ ጭንቀት ለማወቅ ሞክር

ሰለፎች ከሶላት ጋር ያላቸውን ቁርኝትና ሶላትን እንዴት ጠብቀው ይሰግዱ እንደ ነበረ

---

[1] ጠበራኒ ዘግቦታል::አልባኒ ሀሰን ብለውታል::

ለመረዳት ሞክር ። ይህን ማድረግህ የእነሱን አርአያነት እንድትከተል ይዳርገሃልና ።

17. የጌታህን ታላቅነት ሶላት ውስጥ ከመግባትህ በፊት አስብ

ነቢዩ ﷺ ይህን በተመለከተ የሚከተለውን ብለዋል ።

**«إن أحدكم إذا قام يُصلِّي، فإنما يُناجي ربَّه، فلينظر كيف يُناجيه»** [رواه الحاكم وصححه الألباني].

*"አንድ ሰው ሶላትን ለመስገድ ሲቆም ጌታውን ነው የሚያናግረውና፤ እንዴት ከጌታው ጋር እንደሚነጋገር ያስብ ።"*[1]

18. ሶላት ከሰገድክ በኋላ በተደነገጉት ውዳሴዎች ላይ ዘውትር

ከሶላት በኋላ የሚባሉ ከመልዕክተኛው ﷺ የተላለፉ የተለያዩ ውዳሴዎችን (ዚክሮች) በመጠቀም በብዛት አላህን አውሳባቸው ። ይህን ሳትፈጽም ከመስጊድ ለመውጣት አትቿኩል ።

ልዑል የሆነው አላህ ሶላታችንን እሱን በመፍራትና በመተናነስ፤ በተገቢው ሁኔታ የምንሰግድ እና ከሶላታችንም ተጠቃሚ የምንሆን ያድርገን ።

جعلنا الله تعالى وإياكم من المحافظين على الصلاة الخاشعين فيها، المنتفعين بها.

وآخر دعوانا أن الحمد لله ربِّ العالمين

[1] ሀኪም ዘግቦታል። አልባኒ ሶሂህ ብለውታል።

# ሰለፎች ከሶላት ጋር የነበራቸው ቁርኝት[1]

ሰለፎች (ቀደምት ደጋግ አበዎች)- የነቢዩ ሶሀቦች እና ተከታዮቻቸው- ልንከተላቸው የሚገቡ አርአያዎቻችን ናቸው። እኒህ ምርጥ ህዝቦች በየትኛውም የአምልኮ አይነቶች ጠንካራና አምሳያ የሌላቸው ናቸው። ስለዚህ የነሱን ታሪክና ተሞክሮ ማወቁ እጅግ ጠቃሚ ነው። ቀጥሎ የተወሰኑት ከሶላት ጋር የነበራቸውን ቁርኝት እንመለከታለን።

- *ሰኢድ ኢብን ሙሰየብ* ወደ ሰላሳ አመት ያህል በመስጊድ ውስጥ የአንድም ሰው ጀርባ አይተው አያውቁም ። ምክንያቱም እሳቸው ሁሌም በመጀመሪያዉ ሶፍ ይሰግዱ ነበርና ።
- አቡ ሃያን አባቱን ጠቅሶ እንዳስተላለፈዉ፡ - *ረቢዕ ቢን ኸይሰም* በከባድ በሽታ ታሞ ሳለ ወደ መስጊድ እየተጎተተ -እየተመራ- ይወሰድ ነበር ። አላህ በቤትህ ዉስጥ እንድትሰግድ የፈቀደልህ ሲሆን ለምን ይህን ያህል ትጨነቃለህ ? ተብሎ ሲጠየቅ *ሃየ አለ ሶላህ -ወደ ሶላት ኑ-* የሚለዉን የሶላት ጥሪ እየሰማሁ እንዴት እተኛለሁ ?! በመዳህም ቢሆንም መምጣት ከቻላችሁ እንዳያመልጣችሁ ። በማለት መለሰላቸው ።
- ኢብራሂም አተሚሚ አላህ ይዘንለትና እንዲህ ይላል፡ - የመጀመሪያዉን ተክቢራ -ተክቢረተል ኢህራም - ከመድረስ የሚሰላች ሰው ካያቹህ እሱ ሙናፊቅ ነዉና ከሱ ራቁ።
- ሙስዓብ እንዳስተላለፈው፡ - አሚር ኢብን አብደላ በነፍስ ተሞ ሳለ አዛን ሰማና ይዛችሁኝ ወደ መስጊድ ዉሰዱኝ አለ ። አንተ እኮ በሽተኛ ነህና መሄድ የለብህም

[1] ይህ ክፍል የመጽሀፉ አካል አይደለም። ከተለያዩ መጽሀፎች ሰብስቤ ያካተትኩት ነው።

ተባለ። የአላህን ጥሪ ሰምቼ ምላሽ መስጠት የለብኝም በማለት በፍጹም አልቀርም አለ። የመግሪብን ሶላት ነበርና እንዲሰግድ ይዘዉት ወደ መስጊድ ሄዱ ። አንድ ረከዓ እንደሰገደ እዚያዉ ህይወቱ አለፈ ።

- ወኪዕ ኢብን ጀራህ እንዲህ ይላል፡ - *አእመሽ የሰባ አመት አዛዉንት ነዉ ። ነገር ግን አንድ ቀንም ተክቢረተል ኢህራም አምልጦት አያዉቅም ።*
- *መሃመድ* ኢብኑ ሙባረክ እንዳስተላለፈው፡ - ሰዒድ ኢብኑ አብዱልአዚዝ የጀምዓ ሶላት ሲያመልጠዉ ያለቅስ ነበር ።
- *ገሳን የወንድሙን ልጅ ጠቅሶ እንዲህ ብሏል፡* - አባቴ *ተክቢረተል ኢህራም* ሲያመልጠዉ አይቼ አላዉቅም ።
- ዑመር ኢብኑ ኸጣብ አንድ ቀን የአስር ሶላት በጀምዓ ስላመለጠዉ እራሱን በጣም ወቀሰ እና ከፋራ ይሆነው ዘንድ ወደ ሁለት መቶ ሺህ ዲርሃም የሚገመት መሬት ለአላህ ብሎ ሰደቃ ሰጠ ።
- አብደላህ ኢብኑ ዑመር አንድ የጀምዓ ሶላት ካመለጠዉ ÷ የዚያንን ቀን ሙሉ ሌሊት እየሰገደ ያድር ነበር ። አንድ ቀን የመግሪብ ሶላት ስለረፈደበት ሁለት ባሪያዎችን ለአላህ ብሎ ነፃ አወጣ ።
- ኡወይስ አልቀርንይ ዛሬ የሩኩዕ ሌሊት ነዉ ይልና ሌሊቱን ሙሉ በሩኩዕ ያነጋ ነበር። በሚቀጥለዉ ቀን ደግሞ ዛሬ የሱጁድ ቀን ነዉ ይልና ሌሊቱን ሙሉ በሱጁድ ያነጋ ነበር ።
- አልይ ስለ ነብዩ ባልደረቦች ሲናገር፡ - በአላህ እምላለዉ የሙሃመድ ባልደረቦችን የሚያክል በፍፁም አላየሁም ። እነሱም ሱጁድና ቂያምን ከማብዛታቸዉ የተነሳ ፀጉራቸዉ የተቆጣጠረና አቡዋራ በአቡዋራ ሆነዉ ያነጉ ነበር ።

ኢብነ ቀዩም -አላህ ይዘንለትና - እንዲህ ይላል፡- ‹‹በሰጋጆች ዘንድ የሚስተዋሉ እኒህ ስድስት ባህሪያቶች የሙናፊቅ ባህሪ ናቸዉ ::››

1.በመሰላቸት መስገድ

2.ለይዩልኝ መስገድ

3.ጊዜውን አሳልፎ መስገድ

4.ያለ ኹሹዕ መስገድ

5.በሰላት ውስጥ ጥቂትን እንጂ አላህን አለማዉሳት

6.በጀምዓ አለመስገድ

## ሰለፎች በሶላት ውስጥ የነበራቸው ኹሹእ

★ ዘይድ አልአቢዲን ለሶላት ሲቆም ይንቀጠቀጥ ነበር :: ለምንድን ነዉ ተብሎ ሲጠየቅም ማን ፊት እንደምቆምና ማንን እንደማናግር አታዉቁምን ?! ይል ነበር :: አንድ ቀን እሱ በሱጁድ ላይ ሳለ እሳት ቤቱ ዉስጥ ተነሳ :: እሳቱም እስኪጠፋ ድረስ ከሱጁዱ ቀና አላለም ነበር :: እንዴት ቤትህ እየተቃጠለ... !? ተብሎ ሲጠየቅ የቂያማ እሳት ይህቺን እሳት እንድረሳ አደረገኝ ብሎ መለሰ ::

★ አሚር ቢን አብዱልቀይስ ተጠየቀ በሰላት ዉስጥ ነፍስያህን ታናግራለህን አለም አላህ ፊት ስለመቆምና ስለሚገጥመኝ እጣ -ፈንታ ምን እንደሚሆን አናግራታለዉ ::

★ ሙስሊም ቢን የሳር ሶላት ሲሰግድ ምንም ንቅንቅ አይልም :: እንዲሁም ለቤተሰቦቹ ይልም ነበር ‹እኔ ሶላት ስሰግድ የፈለጋችሁትን ማዉራት ትችላላቹ፤ እኔ አልሰማቹህምና ::

* ያእቁብ ቢን የዚድ አልበስሪ ሶላት እየሰገደ የለበሰዉ ጋቢ ተሰርቆበት ሲመለስለት ምንም አያዉቅም ነበር ። እሱ በሰላት ተመስጦ ነበርና ።
* ሙሃመድ ቢን ያእቁብ እንዲህ ይል ነበር፡ - እንደሙሃመድ ቢን ነስር ያማረ ሶላት የሚሰግድ ሰው አልተመለከትኩም ። እሱ ሲሰግድ ዝንብ በአፍንጫዉ ገብታ ታደማው እና ደም ይፈሰዉ ነበር ። ነገርግን እሱ ምንም አይንቀሳቀስም ። አገጩን በደረቱ ላይ አድርጎ የመስገጃ ቦታውን ሲመለከት ላየው የተተከለ እንጨት ይመስል ነበር።

**-ተፈፀመ-**

# በሶላት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው[1]

## የጁመዓ ሶላት

**ጥያቄ፡-** አባቴ እድሜው በመግፋቱ ማየት እና መስማት ያዳግተዋል። በሱ ላይ የጁምዓ እና የጀምዓ ሶላት ግዴታ ይሆንበታልን?

**መልስ፡-** አላህ ሙሚኖችን የጁምዓን ሶላት እንዲሰግዱ አዞዋል፤ ግዴታም አድርጎባቸዋል ። በንግድ ላይ ተሰማርተው የጁምዓን ሶላት እንዳያሳልፉ ከልክሏቸዋል ። አላህ እንዲህ ይላል፡ -

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ ! በጁምዓ ቀን ለሶላት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ንግዳችሁን ትታችሁ ወደ ሶላት ሂዱ ። ይህን ማድረጋችሁ ለናንተ የተሻለ ነው ። የምታውቁ ብትሆኑ።»*[2] መልዕክተኛውም ያለ አሳማኝ ምክኝት (ዑዝር) ከጁምዓ ሶላት የሚቀሩትን አላህ ልባቸውን እንደሚቆለፈው አስጠንቅቀዋል ። «ሰዎች ጁምዓን ከመተው ይጠንቀቁ ። ወይም አላህ በልቦቻቸው ላይ ያትምና ከዘንጉዎች ይሆናሉ ።»3 ሁሉም የሙስሊም ምሁራን የጁምዓ ሶላት ግዴታ መሆኑን ተስማምተውበታል ።

አላህ የአምስት ወቅት ሶላቶችን በጀምዓ መስገድ ግዴታ አድርጎዋል ። በጦርነት ላይ እንኳ በጀምዓ እንዲሰገድ አዟል። በጀምዓ መስገድ ግዴታ ባይሆን ኖሮ በጦርነት ጊዜ ለብቻ እንዲሰገድ ባግራራ ነበር ። ከመልዕክተኛውም የተገኘው ሀዲስም ይህን ያጠናክራል ። *«ህይወቴ በእጁ ባለች ጌታ እምላለሁ ። በርግጥ ማገዶ ተሰብስቦ እንዲቀጣጠል፤ ከዚያም ሶላቱን የሚያሰግድ አንድ ሰው ወክዬ እነዚያ ወደ ጀምዓ ሶላት የማይመጡ ሰዎች ዘንድ ሂጄ ቤታቸውን ለማቃጠል አስቤ ነበር ።»*[4] በሌላ ሙስሊም በዘገበው ሃዲስ ላይ አንድ እውር ሰውዬ ወደ መልዕክተኛው መጥቶ መስጊድ የሚያመጣኝ ሰው የለምና ቤቴ መስገድ ይፈቀድልኛልን ? ብሎ ሲጠይቃቸው ፈቀዱለትና ትንሽ እንደሄደ ጠሩት ። ከዚያም አዛን ትሰማለህ ? ብለው ጠየቁት አዎ ብሎ ሲመልስላቸው እንግድያማ መጥተህ መስገድ አለብህ አሉት።

ወላጅህ አንተ እንዳልከው ሆኖ ወደ መስጊድ መሄድን የሚችል ወይም ወደ መስጊድ የሚወሰደው ሰው የሚያገኝ ከሆነ በሱ ላይ ጁምዓ እና አምስት ወቅት ሶላትን መስጊድ ሂዶ በጀምዓ መስገድ ግዴታ ይሆንበታል። ነገር ግን መሄድ የማይችል ወይም የሚወስደው ሰው የማያገኝ ከሆነ ቤት እንዲሰግድ ተፈቅዶለታል። አላህ በአቅማቹ ያህል ፍሩኝ ብሎዋልና ።

---

[1] ይህ ክፍል የመጽሀፉ አካል አይደለም። ከተለያዩ የፈትዋ መጽሀፎች ሰብስቤ ያካተትኩት ነው።

[2] አል-ጁምዓ፡- 9

[3] ሙስሊም ዘግቦታል።

[4] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግመውታል።

**ጥያቄ**፡- እኔ ነጋዴ ነኝ። በሶላት ሰዓት ንግዴን ትቼ ወደ መስጊድ እሄዳለው። ነገር ግን አባቴ በንግድህ ቦታ ስገድ፤ ወደ መስጊድ አትሂድ ይለኛል። በእንዲህ ያለ ሁኔታ አባቴን መታዘዝ ግዴታ ይሆንብኛል?

**መልስ**፡- መስጊድ ሄደህ መስገድህ ትክክል ነው ። በንግድ ቦታ እንድትሰግድ የሚያዝህ አባተህን መታዘዝ አይገባህም። ምክንያቱም በወንጀል ላይ ለፍጡር መታዘዝ አይቻልምና ። አባትህን በእዝነት መምከር እና የኡለማዎችን ፈትዋ መንገር አለብህ። አላህ ይምራልህ።

**ጥያቄ**፡- አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ጀምዓ መሆን ይችላሉን? ከሆነ ሴቷ የምትቆመው ከወንዱ ጎን ነው?

**መልስ**፡- ጀምዓ መሆን ይችላሉ። ሴቷም ከጎኑ ሳይሆን ከኋላው ትቆማለች። አነስን ጠቅሶ ሙስሊም በዘገበው ሀዲስ ተመሳሳይ ሁኔታ ተገልጾዋልና ። አነስ ይላል፡ - *«አያቴ ምግብ ሰርታ መልዕክተኛው እንዲበሉ ጋበዘቻቸው። መልዕክተኛው በሉና በቤታችሁ ልስገድበት አሉ ። ከዚያም እሳቸውም ከፊት ቆሙ፡ እኔና አን የቲም ልጅ ከኋላ ቆምን ሽማግሌዋ አያቴ ከኋላችን ቆመች ። ሁለት ረከዓ ከሰገድን በኋላ መልዕክተኛው ሄዱ።»* በሌላም መሰል ሀዲስ መልዕክተኛው ኢብን አባስን ከቀኝ ጎን አድርጎ ሰግደዋል ። ሴትንም ብትሆን ማሰገድ ይቻላል ። ነገርግን የአነስን ሀዲስ በመመርኮዝ እሷ ከኋላ መሆን አለባት ። ይህ ሁሉ መሆን ያለበት በሱና ሶላት ነው ። መልዕክተኛው «አዛን ለሚሰማ ሰው መስጊድ ሄዶ ካልሰገደ ሶላቱ ተቀባይነት የለውም ። አሳማኝ ምክንያት ካለው በስተቀር ።» በማለታቸው ፈርድ ሶላት ከሆነ ወንወድየው መስጊድ ሄዶ መስገድ ግዴታው ነው ።

**ጥያቄ**፡- የጀምዓ ሶላትን ትቶ ለብቻ ለመስድ የሚያስችል ምክንያት ምንድን ነው? ፈተና ደርሶበት እየተጨናነቀ ያለ ተማሪ ግዜውን ለመቆጠብ መስጊድ ከመሄድ ይልቅ እዚያው ባለበት መስገድ ይችላል?

**መልስ**፡- ጀምዓን ሶላት ግዴታነት ሊያስነሳ የሚያስችሉት ምክንያቶች፡ - መስጊድ መሄድ የማያስችለው ብርቱ በሽታ፣ መስጊድ ሲሄድ ወይም በመስጊድ ውስጥ በጠላት እጠቃለሁ ብሎ ሚፈራ ከሆነ፣ ብቻውን ሊተኛ የማይችል ክፉኛ የታመመ ሰውን የሚያስታምም ከሆነ እና የመሳሰሉት ። ፈተና ደርሶብኛል ወይም ግዜ አንሶኛል ብሎ የጀምዓ ሶላትን መተው ምክንያት ሊሆን አይችልም ። ጊዜ በጣም ብዙ ነው ። የትምህርት ሰዓትም በጣም ሰፊ ነው ። የጀምዓ ሶላትን መስጊድ ሄዶ መስገድ የሚወስደው ጊዜ ከትምህርት ጊዜ አንጻር በጣም ጥቂት ነው ። ጊዜው ያነሰብህ አንተ ራስህ አባክነነው ነው ። ሶላተል ጀምዓን መስጊድ ሄዶ መስገድ የአላህን ፍራቻ ከሚያስገኙት አምልኮዎች አንዱ ነው ። አላህ ይላል፡ - «አላህን የፈራ ከጭንቅ መውጫ ያበጅለታል፤ ካላሰበው አቅጣጫ ሲሳይን ይለግሰዋል ። በአላህ የተመካ እሱ በቂው ነው።»[1]

[1] አጠላቅ፡ 6-7

## የጁምዓ ሶላት

**ጥያቄ፡-** የጁምዓን ሶላት ለማቆም የሚያስፈልገው አነስተኛው የሰው ቁጥር ስንት ነው? አንዳንድ ሰዎች ከአርባ ሰው በታች ከሆነ (ሰላሳ ዘጠኝ አንኳ ቢሆን) ጁምዓ መስገድ አይቻልም ይላሉ። የኛ መንደር ሰዎች አስራ ሁለት ናቸው። ጁምዓ መስገድ ይችላሉ?

**መልስ፡-** ሙስሊሞች የጁምዓን ሶላት በአከባቢያቸው የመስገድ ግዴታ አለባቸው ። ጁምዓ ሶላት ለማቆም ቅድመ ሁኔታው (ሸርጡ) የጀምዓ መኖር ነው ። ሶስትና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው ካለ ጁምዓን ለመስገድ በቂ ነው። ግዴታ የሆነበት ሰው አርባ አልሞላንም ብሎ በጁምዓ ሶላት ቦታ ዙሁርን መስገድ አይቻልም ። በትክክለኛው የኡሞች አስተያየት ።

**ጥያቄ፡-** ከአረብኛ ቋንቋ ውጭ ኹጥባ ማድረግ ይቻላልን?

**መልስ፡-** በዚህ ጉዳ ላይ ትክክለኛው አስተያየት የጁምዓ ኹጥባን አድማጮች በሚሰሙት ቋንቋ ኹጥባ መደረግ አለበት። አድማጮቹ አረቦች ካልሆኑና አረብኛ የማያውቁ ከሆነ በራሳቸው ቋንቋ ኹጥባ መደረግ አለበት። ሊገነዘቡት የሚችሉት በእንደዚህ ከሆነ ነውና። የኹጥባ አላማ የአላህን ህግጋት ለባሮቹ ማብራራት፤ መግለጽ እና መመሪያ መስጠት ነው። የቁርዓን አንቀጾች ግን በአረብኛ ተቀርተው ከዚያም መቶርጎም አለባቸው። በሰዎች ቋንቋ ኹጥባ መደረግ እንዳለበት የሚከተለው የአላህ ቃል ያመለክታል። *‹‹ከመልዕክተኛ ማንኛውንም ለነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም…* ››[1] በዚህ አንቀጽ አላህ መልዕክት ለሰዎች ሊብራራላቸው የሚችለው በሚረዱት ቋንቋ መሆኑን ገጾዋል፡

**ጥያቄ፡-** ከጁምዓ ኹጥባ በኋላ ኢማሙ ዱዓ ሲያደርግ አሚን ማለት ቢድዓ ነውን?

**መልስ፡-** ይህ ቢድዓ አይደለም ። ኸጢቡ ለሙስሊሞች ዱዓ ሲያደርግ አሚን ማለት የተወደደ ነው ። ነገርግን በአንድ ላይ ከፍ ባለ ድምጽ አይደለም ። መረባበሽና ጩኸት እንዳይኖር ሁሉም በየግሉ ድምጹን ሳያሰማ አሚን ማለት አለበት።

**ጥያቄ፡-** በጁምዓ ቀን ኢማሙ ኹጥባ ሲያደርግ እጅን ማንሳት እንዴት ይታያል?

**መልስ፡-** በጁምዓ ቀን ኢማሙ ኹጥባ ሲያደርግ እጅን ማንሳት የተደነገገ አይደለም ። ቢሽር ቢን መርዋን በጁምዓ ኹጥባ ላይ እጁን ሲያነሳ ሶሃቦች -የነብዩ ባልደረቦች- ተቃውመውታልና። ከዚህ የሚለየው ለዝናብ የሚደረገው ዱዓ ብቻ ነው ። ነብዩ የጁምዓ ኹጥባ እያደረጉ አላህ ዝናብ እንዲያዘልምላቸው እጆቻቸውን አንስተው ዱዓ ሲያደርጉ ሶሃቦችም አብረውዋቸው እጆቻቸውን አንስተው አሚን ብለዋል ። ከዚህ ዉጪ በጁምዓ ኹጥባ ውስጥ በሚደረገው ዱዓ ላይ እጅን ማንሳት ተገቢ አይደለም ።

[1] ኢብራሂም፡- 4

## የተራዊህ ሶላት

**ጥያቄ፡-** የተራዊ ሶላት ሁክሙ ምንድን ነው የረከዓው ብዛትስ ስንት ነውን?

**መልስ፡-** የተራዊህ ሶላት የነብዩ ሱና ነው ። ነብዩ ኢድ ሌሊት መስጊድ ውስጥ ሲሰግዱ ሰዎች ተከትለዋቸው ሰገዱ ። በሚቀጥለው ቀንም እንዲሁ ሲሰግዱ ሰሶች በብዛት ተከትለዋቸው ሰገዱ ። በሶስተኛው ወይም በአራተኛው ቀንም ሰዎች በብዛት ተሰበሰቡ ። ነብዩ ግን ወደ መስጊድ አልሄዱም ። በነጋታው ነብዩ እንዲህ አሉ፡- ‹‹መሰባበሰባችሁን በእርግጥ አይቻለሁ ። ሶላቱ በናንተ ላይ ግዴታ ይሆናል ብዬ በመፍቴ እንጂ ወደ እናንተ ከመውጣት የከለከለኝ የለም ።- ቡኻሪና ሙስሊም ። ይህም በረመዳን ውስጥ ነበር ። የረከዓውን ብዛት በተመለከተ ደግሞ አስራ አንድ ረከዓ ነው ።ዓኢሻ በረመዳን የነብዩ ሶላት እንዴት እንደ ነበረ ተጠይቃ - በረመዳንም ሆነ ከረመዳን ውጪ ከአስራ አንድ ረከዓ ላይ ምንም አልጨመሩም ።›› ብላለች[1] አስራ ሶስት ረከዓ ቢሰገድም ችግር የለውም ። ኢብኑ አባስ የነብዩን ሰላት አስራ ሶስት ረከዓ ነበር ብለዋልና[2] ማለትም የሌሊት ሶላት።

ከዑመር ኢብኑል ኸጣብ በትክክለኛ ሰነድ የተዘገበ አስራ አንድ ረከዓ ሲሆን በሙወጣዕ ኪታብ ዉስጥ ይገኛል ከዚህ ቢጨምርም ችግር የለዉም ። ነብዩ ስለሌሊት ሰላት ተጠይቀዉ ሁለት ሁለት አሉ እንጂ አልገደቡም። ከሰለፎች በዚህ ጉዳይ ላይ በተለያየ መልኩ ተዘግቧል ግን ከነብዩ የተዘገበዉ ብቻ -ማለትም አስራአንድ ወይም አስራሶስት ረከዓ ላይ- መወሰኑ በላጭ ነዉ ። ነብዩም ሆኑ ከኹለፋኡ ራሺዲን አንድም ሃያ ሶስት ረከዓ መስገዳቸዉ በትክክለኛ ዘገባ አልደረሰንም ። ዑመርም የሰገዱት አስራአንድ ረከዓ ነበር ። ዑመር ኡበይ ቢን ከዕብና ተሚም አልዳሪን ሰዎችን አስራ አንድ ረከዓ እንዲያሰግዱ አዘዋቸዋል ። ከዑመር የሚጠበቀዉም ይኸዉ ነበር። የእሳቸዉ ስራ ከነብዩ ሰራ ጋር መጣጣም አለበትና ።

ሶሃቦችም ከአስራ ሶስት ረከዓ በላይ መጨመራቸዉ መዘገቡን የምናዉቀዉ ነገር የለም ። እንደዉም ገሃዱ የዚህ ተቃራኒ ነዉ ። ነው ።ዓኢሻ በረመዳን የነብዩ ሶላት እንዴት እንደ ነበረ ተጠይቃ - በረመዳንም ሆነ ከረመዳን ውጪ ከአስራ አንድ ረከዓ ላይ ምንም አልጨመሩም ።›› ማለቷን አዉስተናል ። የሶሃቦች ኢጅማዕ-ስምምነት ማስረጃ ለመሆኑ ጥርጥር የለዉም ። እንድንከተላቸዉ በነብዩ የታዘዝንባቸዉና የዚህ ኡመት በላጭ የሆኑ ኹለፋኡ ራሺዲን ይገኙባቸዋልና ።

የተራዊህ ሶላት ረከዓ ብዛትና የመሳሰሉት ነገሮች ሰዎች በኢጅቲሃድ ሊለያዩባቸዉ የሚችሉ ጉዳዮች በመሆናቸዉ በሰዎች መካከል ልዩነታቸዉና መቃቃርን ሊያስከትሉ አይገባም ። በተለይም በዚህ ጉዳይ ሰለፎቹም ልዩነት ነበራቸዉ ። በዚህ ጉዳይ ላይ ኢጅቲሃድን በር ዝግ የሚያደርግ ማስረጃ የለም ።

---

[1] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።
[2] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

አንድ አሊም በኢጅቲሃዳዊ ጉዳይ ከርሱ ለተለየዉ ሰዉ ያለዉ አመለካከት ምንኛ ያማረ ነዉ እንዲህ ያለዉ አንተ ከኔ የተለየ ሀሳብ በመያዝህ ተስማምተኸኛል። ኢጅቲሃድን በሚቀበል ጉዳይ ላይ ሁለታችንም ሃቅ ነዉ ብለን የምናምንበትን መከተል እንዳለብን እናምናለን - በዚህ ነዉ ስምምነታችን ። አላህ የሚወደዉን ነገር ያሰራን።

**ጥያቄ፡-** በተራዊህ ሰላት ዉስጥ ኢማሙን ለመከታተል በማለት መእሙሞች ቁርዓን መያዛቸዉ እንዴት ይታያል?

**መልስ፡-** ለዚህ አላማ ብሎ ቁርዓን መያዝ ሱናን መፃረር ነዉ። ይህም በተለያየ መልኩ ይገለፃል።

- በቂያም ላይ ሰዉየዉ ቀኝ እጁን ግራጁ ላይ ማድረጉ ይቀርበታል ።
- አስፈላጊ ላልሆኑ እንቅስቃሴዎች ይዳረጋል ለምሳሌ ቁርዓንን መክፈት መዝጋት በብብት ስር ወይም በኪስ ማድረግና የመሳሰሉት
- እነዚህ እንቅስቃሴዎች የሰጋጁን ትኩረት ያዛባሉ
- ሰጋጁ የስጁድን ቦታ መመልከት ያመልጠዋል ። አብዛኛዎቹ ዑለማዎች እንደሚሉት ደግሞ በሰላት ጊዜ የስጁድን ቦታ መመልከት ሱናና በላጭ ነዉ ።

ይህን የሚያደርግ ሱዉ -ቁርዓን የሚይዝ ልቡ ሌላ ቦታ ካሰበ ሶላት ዉስጥ መሆኑን ሊረሳም ይችላል ። በአንፃሩ ቀኝ እጁን በግራ እጁ ላይ አድርጎ እና አንገቱን ሰብሮ ወደስጁድ ቦታ እየተመለከተ በ ኹሹዕ ከቆመ ግን ልቡን ለመሰብሰብና ከኢማሙ ኃላ በመስግድ ላይ መሆኑን ለማስታስ በጣም ቅርብ ነዉ ።

### የዒድ ሶላት

**ጥያቄ፡-** የኢድ ሶላት ሁክም ምንድን ነው?

**መልስ፡-** በእኔ አመለካከት የኢድ ሶላት በያንዳንዱ ሰው ላይ ግዴታ (ፈርዱ ዐይን) ነው። ወንዶች መተው አይፈቀድላቸውም። ነብዩ ﷺ አዘውበታልና። እንዲያውም ከቤት የማይወጡ ልጃገረዶችም ሳይቀሩ ለኢድ ሶላት እንዲወጡ አዘዋል ። የወር አበባ ያለባቸውንም ሴቶች ወደ ኢድ ሶላት እንዲሄዱ አዘዋል ። ነገርግን ከመስገጃው ቦታ ገለል ብለው ይቀመጣሉ ። ይህ የሚያሳየው ጉዳዩ ጠንከር ያለ መሆኑን ነው ። ስለዚህ ይህ አቋም ይበልጥ ተቀባይነት ያለው ከመሆኑም በላይ የሸይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያም አቋም ነው ። ነገር ግን ልክ እንደ ጁምዓ ሶላት ሁሉ ካመለጠ ቀዷ አይወጣም ። ቀዷ ማውጣት ግዴታ እንደሚሆን የሚያሳይ ማስረጃ የለምና። በምትኩም ሌላ ሶላትም አይሰገድም።

ሙስሊም ወንድሞቼን የምመክራቸው አላህን እንዲፈሩና ይህንን መልካም ስራ፡ - ዱዓን፣ የሰዎች እርስ በርስ መተያየትን፤ መቀራረብን እና መዋደድን ያካተተ ሶላት እንዳይተውት ነው ። ሰዎች የማይጠቅም ወይም ጨወታ ብቻ ለሆነ ስብሰባ ቢጠሩ እየተቻኮሉ ይሄዳሉ ። ታዲያ ይህንን ከአላህ ምንዳ ወደ ሚያገኙበት እና ነብዩ ﷺ ወደ ጠሯቸው የሶላት ግብዣ ይበልጥ ተቋክለው መሄድ አልነበረባቸውምን !?

ሴቶች ግን ለዒድ ሶላት ከወጡ ወንዶች ካሉበት ቦታ ራቅ ብለው መቀመጥ አለባቸው ። ለዚህ ሶላት ሲወጡም ተውበውና ሽቶ ተቀብተው ወይመም ተገላልጠው መውጣት የለባቸውም ። ነብዩ ሴቶች ለኢድ ሶላት እንዲወጡ ሲያዟቸው ሴቶቹ ነብዩን ‹‹የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! አንዳዶቻችል ጅልባብ አናገኝም›› ብለው ሲጠይቋቸው ነብዩም ‹‹እህቷ ከጅልባቧ ታልብሳት›› ብለው መሉሱላቸው፡፡[1] ጅልባብ አባያ የሚመስል ሙሉ ሰውነትን የሚሸፍን ልብስ ነው ። ሴት ጅልባብ ለብሳ መውጣት ግዴታዋ እንደሆነ ይህ ሀዲስ ያስረዳል። ምክንያቱም ነብዩ - ጅልባብ የሌላት ሴት ምን ማድረግ እንዳለባት ሲጠየቁ ያላትን ነገር ለብሳ ትውጣ አላሉም፤ *‹‹እህቷ ከጅልባቧ ታልብሳት ።››* ነው ያሉት ። ይህም ካሏት ጅልባቦች አንዱን ትስጣት (ታውሰዋት) ማለት ነው።

ኢማሙ ኹጥባ ሲያደርግ ሴቶች የማይሰማቸው ከሆነ ለነሱም ለብቻቸው ኹጥባ ሊያደርግላቸው ይገባል ። የሚሰሙ ከሆነ ግን መድገም አያስፈልግም ። ይሁን እንጂ በኹጥባው መጨረሻ ሴቶችን የሚመለከት መልዕክት በማካተት ሴቶችን መገሰጽ፣ መምከርና ማስታወስ የተወደደ ነው ። ነቢዩ - ለወንዶች በኢድ ሶላት ላይ ኹጥባ ካደረጉ በኋላ ወደ ሴቶች በመሄድ ይገስጹና ይመክሩ ነበርና ።

**ጥያቄ፡-** የሁለቱ ኢድ ሶላቶች አሰጋገድ እንዴት ነው?

**መልስ፡-** የኢድ ሶላቶች አሰጋገድ ኢማሙ ተገኝቶ ሁለት ረከዓ ያሰግዳል ። መጀመሪያ ለኢህራም ተክቢራ ያደርጋል። ከዚያም ስድስት ጊዜ ተክቢራ ያደርጋል ። ከዚያም ፋቲሃ ቀጥሎም የሱረቱለረ ቃፍ ምዕራፍ ይቀራል። ይህ መጀመሪያ ረከዓ ላይ ነው ። ለሁለተኛው ረከዓ ሲነሳ ተክቢራ አድርጎ ይቆማል ። ከቆመ በኋላ አመምስት ጊዜ ተክቢራ ያደርጋል ። ከዚያም ፋቲሃን ቀጥሎም ሱረቱል ቀመርን ይቀራል ። እነዚህን ሁለቱን ሱራዎች-ቃፍና አልቀመርን- ነብዩ- በኢድ ሶላቶች ይቀሯቸ ነበር ።[2] ከፈለገም በአንደኛው ረከዐ ላይ ‹‹ሰቢህ ኢስመ-ረቢከል አዕላ››ን በሁለተኛው ረከዓ ላይ ደግሞ ‹‹ሀል-አታከ ሀዲሱል ጋሺያ››ን መቅራት ይችላል ።[3] የጁምዓና የኢድ ሶላቶች ሁለት ሱራዎችን ይጋራሉ ። በሁለት ሱራዎች ደግሞ ይለያያሉ ። የሚጋሯቸው ሁለቱ ‹‹ሰቢህ›› እና ‹‹አል -ጋሺያህ›› ናቸው ። የሚለያዩባቸው ሁለቱ ደግሞ ‹‹ቃፍ›› እና ‹‹አል -ቀመር›› ለኢድ ብቻ ሲሆኑ ሱረቱል ‹‹ጁምዓ›› እና ‹‹አል -ሙናፊቁን›› ለጁምዓ ሶላት ብቻ መሆናቸው ነው ። ኢማሙ እነዚህን ሱራዎች በመቅራት ሱናውን መተግበርና ሰዎችንም ማስለመድ ይጠበቅበታል። ከሶላት በኋላ ኹጥባ ያደርጋል። ኢማሙ ነብዩ - እንዳደረጉት በኹትባው ውስጥ ሴቶች ብቻ የሚመለከት በመጨመር መፈጸም ያለባቸውን ትዕዛዛት እንዲፈጽሙ እና መከልከል ካለባቸው ነገሮች እንዲከለከሉ ሊመክራቸው ይገባል ።

---

[1] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

[2] ሙስሊም ዘግቦታል።

[3] ሙስሊም ዘግቦታል።

## የሶላቱል ጀናዛ አሰጋገድ

**ጥያቄ፡-** የሶላቱል ጀናዛ አሰጋገድ ስርዓት እንዴት ነው?

**መልስ፡-** የሶላቱል ጀናዛ አሰጋገድ፡ - ጀናዛው ወንድ ከሆነ ከኢመዘሙ ፊት ለፊት ይደረግና ኢማሙ በጀናዛው ራስ አቅጣጫ ይቆማል ። ጀናዛው የህጻንም ይሁን የአዋቂ ልዩነት የለውም ። በራሱ አቅጣጫ ቆሞ የመጀመሪያውን ተክቢራ ያደረርጋል፤ ፋቲሃ ይቀራል፤ ከዚህ ቀጥሎ አጭር ሱራ ቢቀራ ችግር የለውም ። እንዲያውም አንዳንድ ኡለሞች ሱና መሆኑን ይናገራሉ ። ከዚያም ሁለተኛውን ተክቢራ አድርጎ በነብዩ - ላይ ሰለዋትን ያወርዳል ። ይህም፡ - «አላሁመ ሰሊ አላ ሙሀመዲን ወአላ ኣሊ ሙሀመዲን ከማሰለይተ አላ ኢብራሂመ ወአላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢነከ ሀሚዱን መጂድ ። አላሁመ ባሪክ ኣላ ሙሀመዲን ወአላ ኣሊ ሙሀመዲን ከማ ባረክተ አላ ኢብራሂመ ወአላ ኣሊ ኢብራሂመ ኢነከ ሀሚዱን መጂድ ።›

ከዚያም ሶስተኛውን ተክቢራ ያደርግና ከነብዩ ﷺ የተላለፉትን ዱዓ በመጠቀም ለሟቹ ዱዓ ያደርጋል ። ከዱዓዎቹም መሀል የሚከተሉት ይገኙበታል ።

*«አላህ ሆይ ! በህይወት ላለንም ለሞቱትም፤ እዚህ ላለነውም ሆነ ሩቅ ላሉትም፤ ለትልቆቻችንም ሆነ ለህጻናቶቻችን፤ ለወንዶቻችንም ሆነ ለሴቶቻችን ምህረትን አድርግ ። አላህ ሆይ ! ከኛ ውስጥ በህይወት የኖርከውን በኢስላም ላይ አኑረው ። የገደልከውንም በኢማን ላይ ግደለው ።›*

*‹አላህ ሆይ ! ምህረት አድርግለት፤ እዘንለት፣ ጤንነት ስጠው፣ይቅር በለው፣ ማረፊያውን አሳምርለት፤ መግቢያውን አስፋለት፤ በውሃና በበረዶ እጠበው፤ ነጭ ልብስ ከቆሻሻ እንደ ሚጠራው እሱንም ከወንጀሉ አትራው። አላህ ሆይ ! ምንዳውን አታሳጣን፤ ከርሱም - ከሟቹም- በኋላ አታጥምመን፤ ለኛም ለርሱም ምህረትን አድርግለን።›*

ከዚህም ሌላ ከነብዩ ﷺ የተላለፉትን ሌሎች ዱዓዎች ሊያደርግ ይችላል ። ከዚያም አራተኛውን ተክቢራ ያደርጋል። ከፊል ኡለሞች ከዚህ ተክቢራ በኋላ #ረበና ኣቲና ፊዱንኛ ሀሰነተን ወፊል አኺረቲ ሀሰነተን ወቂና አዛበናር ማለት አለበት ብለዋል ። አምስተኛ ተክቢራ ቢያደርግም ችግር የለውም ። ከነብዩ ﷺ ተገኝቶዋልና። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ አምስት ተክቢራ ማድረግ ይገባል ። ማንም ሰው ከነብዩ ﷺ የተገኘውን ነገር ከሳቸው በተገኘው መሰረት መፈጸም ይገባዋል ። ሁለቱንም አይነት አሰጋገድ በማፈራረቅ መጠቀም አለበት ። በአብዛኛው የሚደረገው ግን አራት ተክቢራ ነው ። ከዚያም ወደ ቀኝ ብቻ አንዴ ያሰላምታል። ሟች ሴት ከሆነች ግን ኢማሙ የሚቆመው በመሀሏ አቅጣጫ ነው ። አሰጋገዱ ግን ልዩነት የለውም። ብዙ ጀናዛዎች ከሆኑ በጾታና በእድሜ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይገባል ። ከኢማሙ ቀጥሎ ፊትለፊት መደረግ ያለበት የአዋቂ ወንዶች ሬሳ ነው ። ቀጥሎ የወንድ ህጻናት ሬሳ፣ ቀጥሎ የአዋቂ ሴቶች

ሬሳ ከዚያም የሴት ህጻና ሬሳ ነው ። በዚህ ቅደም ተከተል ይቀመጣል ። የኢማሙ መቆሚያ በተደነገገው ቦታ እንዲሆን የወንዶች ራስ በሴቶች መሀል አካል አቅጣጫ ይደረጋል ።
እዚህ ላይ አንድ የማስገነዝበው ነገር አለኝ ። አንዳንድ የማያውቁ ሰዎች ጀናዛውን ያመጡት ሰዎች ከኢማሙ ጋር መቆማቸው የሚመረጥ ይመስላቸዋል ። እንዲያውም አንዳንዶቹ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰው ከኢማሙ ጋር መቆሙ ግዴታ ነው የሚል ድምጽ አላቸው ። ይህ ስህተት ነው ። ምክንያቱም ሱናው ኢማሙ ለብቻው መሆኑ ነው ። ጀናዛውን ያመጡት ሰዎች ከአንደኛው ሶፍ ላይ ቦታ ካጡ በኢማሙና በአንደኛው ሶፍ መካከል ተሰልፈው ይቁሙ ።

## የመንገደኛ ስለጋገድ

**ጥያቄ፡-** መንገደኛ የሆነ ሰው በሄደበት ሀገር ከሶስት እስከ ስድስት ቀን የሚቆይ ከሆነ ሶላቱን ማሳጠር ይችላልን? አንድ አመት ቢሆንስ?
**መልስ፡-** መንገደኛው (ሙሳፊሩ) የሚሄደው ከ4 ቀን በላይ ለመኖር ከሆነ ሶላትን ማሳጠር አይችልም ። ከዚያ በታች ከሆነ ግን ይችላል ። ተየሙም ማድረግ ከፈለገም በንጹህ አፈር ማድረግ ይችላል ። አላህ እንዲህ ብሏል፡፡ «ንጹህ በሆነ አፈር ተየሙም አድርጉ፡፡ እጆቻችሁንና እግሮቻችሁን አብሱበት ፡፡»[1]
**ጥያቄ፡-** መንገደኛ የሆነ ሰው ቀስርን[2] ያለ ጀምዕ[3] ወይም ጀምዕን ያለ ቀስር መስገድ ይችላልን?
**መልስ፡-** ቀስርን ያለ ጀምዕ ወይም ጀምዕን ያለ ቀስር መስገድ ይቻላል ። ነገርግን ለመንገደኛ ሶላትን ማሳጠር ሙሉ ከመስገድ የተሻለ ነው ። ጀምዕም ቢሆን እንዲሁ ። አላህ ግዴታ ያደረገው ነገር ሲተገበር እንደሚወደው ሁሉ ያቃለለው ነገር ሲተገበር ይወዳልና ። መልዕክተኛው ﷺ ይተገብሩት እንደነበረ ተገልጾዋል ።
**ጥያቄ ፡-** መንገደኛ የሆነ ሰው አዛን ማድረግ ይጠበቅበታልን?
**መልስ፡-** ይህ ጉዳይ ኺላፍ (ልዩነት) አለበት፡፡ ትክክለኛው ግን አዛን ማድረግ በሙሳፊሮች ላይም ግዴታ መሆኑ ነው ። ነቢዩ ﷺ ለማሊክ ቢን አልሁወይርስና ለጓደኞቹ ሶላት ሲደርስ አንዳችሁ አዛን ያድርግላችሁ ብለዋልና4፡፡ በወቅቱ እነሱ ወደ ነቢዩ ﷺ የመጡ ልዑካን ሲሆኑ ወደ ሀገራቸውም ለመመለስ እየተዘጋጁ ያሉ ሙሳፊሮች ነበሩ ። ነቢዩም ﷺ በሀገር እያሉም ሆነ ሙሳፊር ሆነው አዛንም ሆነ ኢቃምን ትተው አያውቁም፡፡ መንገድ በሄዱበት ቦታ ሁሉ አዛን ይደረግ ነበር ። ቢላልን አዛን እንዲደረግ ያዙ ነበር ።
**ጥያቄ፡-** ሙሳፊር የሆነ ሰው በሀገሩ ነዋሪ (ሙቂም) የሆነ ኢማም በሚያሰግደው ሶላት፡- የመጨረሻውን ሁለት ረከዓ ከደረሰበት፤ በቀስር ኒያ ከኢማሙ ጋር ማሰላመት ይችላልን?

---

[1] ኒሳዕ፡- 43
[2] አራት ረከዓ የሆኑ ሶላቶችን -ዙሁር፣ አስር እና ኢሻዕን- ወደ ሁለት ረከዓ አሳጥሮ መስገድ፡፡
[3] ሁለት የተለያዩ ሶላቶችን -ዙሁርና አስርን እና መግሪብና አሻዕን- ሰብስቦ በአንድ ጊዜ መስገድ፡፡
[4] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

**መልስ፡-** ሙሳፊር የሆነ ሰው የሀገር ነዋሪ (ሙቂም) በሆነ ኢማም ተከትሎ ከሰገደ ሶላቱን ማሳጠር አይችልም። ነቢዩ ﷺ ጠቅለል ባለ መልኩ «የደረሳችሁትን ስገዱ ያመለጣችሁን ሙሉ » ብለዋልና[1] ። ስለዚህ ሙሳፊር ከሙቂም ኢማም ጋር ሁለት የመጨረሻዎችን ረከዓ ከሰገደ ኢማሙ ካሰላመተ በኋላ ቀሪዎቹን ረከዓዎች ማሟላት አለበት ። ሁለቱን ረከዓ ብቻ ሰግዶ በማሳጠር ከኢማሙ ጋር ማሰላመት አይችልም። ወላሁ አዕለም።

### የማይሰግድ ሰው ሁክም

**ጥያቄ፡-** ቤተሰቦቹ ሙስሊም ሆነው ሳለ እሱ የማይሰግድ ሆኖ የሞተ ሰውን፡- ሬሳ ማጠብ፣ መከፈን፣ ሶላተል ጀናዛ በሱ ላይ መስገድ፣ መቅበር እና ለሱ ዱዓ ማድረግ እንዴት ይታያል?

**መልስ፡-** ለአቅመ አዳም ደርሶ እና እውቀቱ ኖሮት የማይሰግድ ሆኖ የሞተ ሰው ካፊር (ከሀዲ) ነው። ሬሳው አይታጠብም፣ አይሰገድበትም፣ በሙስሊሞች መቃብር ላይ አይቀበርም ። የውርስ ገንዘቡንም ሙስሊም ቤተሰቦቹ ሊወርሱት አይችሉም። ገንዘቡን የሙስሊሞች ግምጃ ቤት (በይቱል ማል) ይወርሰዋል። ትክክለኛው የኡለሞች አቋም ይህ ነው። የሚከተሉትን መረጃዎች ከግንዛቤ በማስገባት ። ሶሂህ በሆነ ሀዲስ መልዕክተኛው ﷺ እንዲህ ብለዋል ። «በሰውየውና በሽርክ ወይም ኩፍር (ክህደት) መሀል ያለው ልዩነት ሶላትን መተው ነው።»[2] እንዲሁም ኢማሙ አህመድ በዘገቡት ሶሂህ በሆነ ሀዲስ መልዕክተኛው ﷺ እንዲህ ብለዋል፡ - «በኛና በነሱ (በከሀዲያን) መሀል ያለው (መለያ) ቃልኪዳን ሶላት ነው ። ሶላትን የተወ በርግጥ ካደ ።» ታቢዒይ የሆነው አብደላ ብን ሽቂቅ -አላህ ይዘንለትና- ቡረይዳን ጠቅሶ እንዲህ ብሏል፡ - «የመልዕክተኛው ﷺ ባልደረቦች ሶላት ሲቀር ማንኛውንም (ኢባዳ) መተው ክህደት ነው ብለው አያስቡም ነበር ።» ይህን መሰል ሀዲስ እና የሰሃቦች ንግግር ብዙ አለ ። ይህ ፍርድ የሶላትን ግዴታነት አምኖ በመሰላቸት ወይም በሌላ ምክንያት ሶላትን ለሚተው ሰው ነው ። የሶላትን ግዴታነት የካደ ሰው ካፊር እና ከእስልምና ሙሉ በሙሉ ያፈነገጠ (ሙርተድ) መሆኑን ሁሉም የሙስሊም ምሁራን በአንድነት ተስማምተዋል ።

አላህ የሙስሊሞችን ሁኔታ እንዲያስተካክለው፤ ወደ ቀጥተኛው መንገድ እንዲመራቸው እንለምነዋለን ። እሱ ሰሚ እና ተቀባይ ነውና።

**ጥያቄ፡-** ሴትየዋ ባሏ ሶላት አይሰግድም። ከርሱ ልጅ ወልዳለች። ከርሱ ጋር መኖሯ እንዴት ይታያል? ለማይሰግድ ሰው መዳርስ ይቻላል?

**መልስ፡-** አንዲት ሴት በጀምዓም ሆነ ለብቻው ከማይሰግድ ሰው ጋር ከተጋባች ኒካሁ ውድቅ ነው ። ሶላት የማይሰግድ ሰው ካፊር ነውና ። የአላህ ቁርዓን፣ የነብዩ ﷺ ሱና እና የሶሀቦች አስተያየትም ይህን

---

[1] ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

[2] ሙስሊም ዘግቦታል።

ያመላክታል። አብደላ ኢብን ሽቂቅ «የነቢዩ ሶሃቦች ከሶላት ውጪ መተው የሚያስከፍር ሌላ ስራ አለ የሚል እምነት አልነበራቸውም ።»[1] ብሏል። ካፊር ደግሞ ሙስሊም ሴት ሀላል አትሆንለትም ። አላህ ይላል፡ - *‹‹አማኞች መሆናቸውን ካወቃችሁ ወደ ከሀዲዎች አትመልሷቸው እነርሱ (ሴቶቹ) ለነርሱ የተፈቀዱ አይደሉምና። እነርሱም (ወንዶቹ) ለነርሱ አይፈቀዱምና።»*[2]

ሶላት የተወው ኒካህ ካሰረ በኋላ ከሆነ ኒካሁ ይፈርሳል ። ተውበት አድርጎ ወደ እስልምና እስካልተመለሰ ድረስ። ከርሱ የወለደቻቸው ልጆች ቢኖራትም እንኳ ። ሰውየው በዚህ ሁኔታ ላይ ሆኖ በልጆቹ ምንም መብት የለውም።

ሙስሊም ወንድሞቼን እና እህቶቼን ሴት ልጃችውን ወይም በቁጥጥራቸው ስር ያሉትን ሴት ልጆችን ለማይሰግድ ሰው እንይድሩ አስጠነቅቃቸዋለሁ ። ይህ ከባድ አደጋ ነውና ። በዚህ ጉዳይ ላይ ዘመድንም ሆነ ጓደኛን መፍራት የለባቸውም። ሁላችንም አላህ እንዲመራን እማጸነዋለሁ።

**ጥያቄ፡-** ሶላት በማይሰግዱ ልጆች ላይ ቤተሰብ ምን ግዴታ አለበት?

**መልስ፡-** አንድ ቤተሰብ የማይሰግዱ ልጆች ካሏቸው እንዲሰግዱ የማስገደድ ግዴታ አለባቸው። ይህም በቃልና በትዕዛዝ ወይም በመምታት ሊሆን ይችላል። ነቢዩ ﷺ «…ልጆቻችሁ አስር አመት ሲሞላቸው (ካልሰገዱ) እንዲሰግዱ ምቷቸው።» ብለዋልና[3]። መምታቱ ካልጠቀመ (ሀገሪቷ በሸሪዓ የምትተዳደር ከሆነ) ለሚከተለው የመንግስት አካል ማሳወቅ ነው። ዝም ማለት አይፈቀድም። ዝም ማለት መጥፎን ነገር (ሙንከርን) ተስማምቶ እንደመቀበል ይቆጠራል። ሶላትን መተው ከኢስላም የሚያስወጣ ኩፍር ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ከሞተ ሬሳውን ማጠብ፤ በርሱ ላይ መስገድ እና በሙስሊሞች መካነ መቃብር መቅበር አይፈቀድም። አላህ ሰላምን ያጎናጽፈን።

## የተለያዩ ርዕሶች

**ጥያቄ፡-** ለብቻው የሚሰግድ ሰው አዛንና ኢቃም ማድረጉ እንዴት ይታያል?

**መልስ፡-** ለብቻው የሚሰግድ ሰው አዛን እና ኢቃም ማድረጉ ሱና እንጂ ግዴታ አይደለም ። ከአጠገቡ በአዛኑ የሚጠራው ሰው የለምና። ነገርግን አዛንም ሆነ ኢቃም አላህን ማውሳትና ማላቅ እና ራስንም ወደ ሶላት እና ፈላህ (ድል) መጥራት ስለሆነ ማድረጉ ሱና ነው፡ አዛን የተወደደ ለመሆኑ የሚከተለው የኡቅባህ ቢን ኣሚር ሀዲስ ያመላክታል። ኡቅባህ እንዲህ አለ፡ - ነብዩ ﷺ እንዲህ ሲሉ ሰማኋቸው፡ - ተራራ ጫፍ ሆኖ ለሶላት አዛን በሚያደርግ እረኛ ጌታህ ይገረማል ። ይላልም፡- «ባሪያዬ ለሶላት አዛን እና ኢቃም ሲያደርግ፡ - እንዴት ይፈራኛል፤ ለባሪያዬ ምህረትን አድርጌያለሁ፤ ጀነትንም አስገባዋለሁ ።»[4]

---

1 ቲርሚዚይ ዘግቦታል።

2 ሙምተሂና፡- 10

3 አህመድ እና አቡዳውድ ዘግበውታል።

4 አህመድ እና አቡዳውድ ዘግበውታል።

**ጥየቄ፡-** አላህ ሶላት ከመጥፎ እና ከአጸያፊ ተግባራት ትከላከላለች እያለ፤ ከመጥፎ ተግባራት አንዱ የሆነውን መጠጥ ማታ ማታ እየጠጣ ንጋት ላይ ሶላት የሚሰግድ ሰው ሶላቱ ተቀባይነት አለው?

**መልስ፡-** ንጽህናውን፣ የሶላቱን ሸርጦች፣ ግዴታዎች እና ማዕዘኖች አሟልቶ የሰገደ እንደሆነ ሶላቱ ተቀባይነት አለው ። የሶላቱን ምንዳ ያገኛል ። በመጠጣቱ ወንጀለኛ ነውና ይቀጣበታል ። እንዲህ አይነት ሰው ጥሩንና መጥፎን የሚቀላቅሉ ከተባሉት ውስጥ ነው ። አላህ እንዲህ ይላል፡- «የብናኝ ያህል ጥሩ ስራን የሰራ ይመነዳበታል። የብናኝ ያህል መጥፎ ስራን የሰራ ይመነዳበታል ።»[1]

**ጥያቄ፡-** እኔ አስራ ስምንት አመት እስኪሞላኝ ድረስ ሶላት አልጀመርኩም ነበር። አሁን አልሀምዱሊላህ በስርዓቱ እሰግዳለሁ ። ጥያቄዬ ሳልሰግድ ላሳለፍኩት ሶላት ቀዷ[2] ማውጣት አለብኝ? ከሆነ ከስንተኛው አመቴ ጀምሮ ነው ቀዷ ማወጣው?

**መልስ፡-** ላለፈው አላህን ምህረትን እንዲለግስሽ ዱዓ አድርጊ ። ቀዷ ማውጣት አይጠበቅብሽም ። ሶላትን መተው ክህደት ነው ። መልዕክተኛው በማለታቸው «በኛና በነሱ (ከሀዲያን) መሀል ያለው (መለያ) ቃል ሶላት ነው። የተወ በርግጥ ካደ ።» ሌሎችም መሰል ሀዲሶች አሉ ። የክህደት ከፋራው (መቀጣጫው) ተፀፅቶ ወደ አላህ ተውበት በማድረግ በጥሩ ስራ ላይ መጠንከር ነው ። አላህ እንዳለው፡- «ተውበትን አድርጎ ጥሩ ስራን በመስራት ለተመራ እኔ ምህረትን ለጋሽ ነኝ ።»[3]

**ጥያቄ፡-** ሰውየው ለሁለት ወር ያህል ራሱን አያውቅም ነበር። አልፆመም አልሰገደም። ምን ማድረግ አለበት?

**መልስ፡-** ራሱን ስለማያውቅ ምንም ግዴታ አይሆንበትም ። ነገር ግን አላህ ካዳነው ረመዷንን ቀዷ ማውጣት አለበት። የአላህ ውሳኔ ሆኖ በዚያው ከሞተም ምን የለበትም ። ችግሩ ቀጣይነት ያለው ከሆነ ግን የሱ ሀላፊ ከሱ ላይ ረመዷንን ሙሉ በየቀኑ አንዳንድ ደሃ ይመግባል ።

ሶላትን በተመለከተ፡- ቀዷ ማውጣት አለበት የለበትም በሚል ኡለሞች በሁለት ተከፍለዋል ።

አንደኛው፡- የጁምሁር (የብዙሃን ኡለማ) አስተያየት ሲሆን ይህም ቀዷ ማውጣት የለበትም የሚል ነው ። ምክንያቱም ኢብን ኡመር አንድ ቀንና ሌሊት ራሱን ስቶ በነበረበት ጊዜ የሶላቱን ቀዷ አላወጣም ነበር ።

ሁለተኛው፡- ቀዷ ማውጣት አለበት የሚል ሲሆን ከሀንበሊይ መዝሀብ ተከታዮች የኂለኞቹ የያዙት አቋም ነው። አል ኢንሳፍ በተሰኘው መጽሀፍ ውስጥ አማር ብን ያሲር ለሶስት ቀነናት ራሱን ስቶ በነበረበት ጊዜ የሶላቶቹን ቀዷ ማውጣቱ ከራሱ ተዘግቧል የሚል ሰፍሯል ።

**ጥያቄ፡-** የሆነ ሰው ኢሻ ሶላት ለመስገድ መስጊድ ሲገባ መግሪብ አለመስገዱን አስታወሰ። ምን ማድረግ አለበት?

---

[1] ዘልዘላህ፡8

[2] የሶላትን ዕዳ መክፈል።

[3] ጣሃ፡ 82

**መልስ፡-** የኢሻ ሶለት ሲጀመር መስጊድ ከገባህ እና መግሪብ አለመስገድህን ካስታወስክ፤ መግሪብን በመነየት ኢሻ ሶላት ከሚሰግዱት ጀምዓ ጋር ትሰግዳለህ፤ ኢማሙ ለአራተኛ ረከዓ ሲቆም አንተ በሶስተኛ ረከዓ ላይ ተቀምጠህ ኢማሙ አራተኛ ረከዐ ሰግዶ እስኪመጣ ድረስ ትጠብቀዋለህ ። ከዚያም አብረኸው ታሰላምታለህ ። ለብቻ አሰላምተህም የቀረውን የኢሻ ሶላት ተነስተህ ከኢማሙ ጋር መስገድም ትችላለህ ። የኢማሙና የመዕሙም መለያየት በእንዲህ ያለ ጊዜ ጉዳት የለውም ። በትክክለኛው የኡለሞች አስተያየት ። መግሪብን ለብቻህ ሰግደህ ከዚያም የደረስክበትን ያክል ከጀምዓ ጋር ኢሻን ብትሰግድም ትችላለህ ።

**ጥያቄ፡-** ሱና ሶላት የሚስግድ ሰውን በመከተል ፈርድ ሶላትን መስገድ ፍርዱ ምንድን ነው? ለምሳሌ ኢሻዕን ተራዊ ከሚሰግድ ሰው ጋር መስገድ።

**መልስ፡-** ተራዊህን ከሚሰግድ ሰው ተከትሎ ኢሻዕን መስገድ ችግር የለውም ። ይህ ነገር እንደሚቻል ኢማሙ አህመድ በጽሁፉ አስፍሯል ። ሙሳፊር ከሆነና ኢማሙን በመጀመሪያ ረሀዓ ከደረሰበት አብሮት ያሰላምታል ። ካልሆነ ግን የቀረውን ተነስቶ ያሟላል ።

**ጥያቄ-** አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ጀምዓ መሆን ይችላሉን? ሴቷ ከወንዱ ጎን መቆምስ ትችላለች?

**መልስ፡-** ጀምዓ መሆን ይችላሉ ። ሴቷ ከጎኑ ሳይሆን ከኋላው ትቆማለች ። አነስን ጠቅሶ ሙስሊም በዘገበው ሀዲስ ተመሳሳይ ሁኔታ ተገልጾዋልና ። አነስ ይላል፡- « አያቴ ምግብ ሰርታ መልዕክተኛው ﷺ እንዲበሉ ጋበዘቻቸው። መልዕክተኛው ﷺ በሉና በቤታችሁ ልስገድበት አሉ ። ከዚያም እሳቸው ከፊት ቆሙ እኔና አንድ የቲም ልጅ ከኋላ ቆምን ሽማግሌዋ አያቴ ከኋላችን ቆመች ። ሁለት ረከዓ ከሰገድን በኋላ መልዕክተኛው ﷺ ሄዱ።» በሌላም መሰል ሀዲስ መልዕክተኛው ﷺ ኢብን አባስን ከቀኝ ጎን አድርገ ሰግደዋል ። ሴትንም ብትሆን ማስገድ ይቻላል ። ነገርግን የአነስን ሀዲስ በመመርኮዝ እሷ ከኋላ መሆን አለባት ። ይህ ሁሉ መሆን ያለበት በሱና ሶላት ነው ። መልዕክተኛው ﷺ «አዛን ለሚሰማ ሰው መስጊድ ሄዶ ካልሰገደ ሶላቱ ተቀባይነት የለውም። አሳማኝ ምክንያት ካለው በስተቀር ።» በማለታቸው ፈርድ ሶላት ከሆነ ወንወድየው መስጊድ ሄዶ መስገድ ግዴታው ነው ።

**-ተፈፀመ-**

- إدارة الأوقاف الخيرية

- قسم تطوير المناهج الدّراسية

## عنوان المركز

☎ +251112781893

Fax: +251112779660

E-mail: info@nesiha.org

www.nesiha.org

ADDIS ABABA

ETHIOPIA

- مركز تحفيظ القرآن الكريم (للبنين وللبنات)
- مركز تعليم القرآن الكريم وتربية الأطفال
- قسم كفالة الدّعاة والمدرسين ودعم المدارس وتطوير المناهج الدّراسية
- المكتبة العلميّة العامّة
- مركز الدّعوة عبر الإنترنت
- قسم تعليم الصّم بلغة الإشارة
- قسم تثقيف طلبة العلم الشرعي من خريجي الحلقات العلمية أكاديميا
- قسم عمارة المساجد
- قسم كفالة الدّعاة والمدرسين

**وبعون الله تعالى حقق المركز إنجازات مهمّة خلال وقت قصير بتخطيط استراتيجية عامّة للدّعوة محورها الأساسي نشر الدّين بمفهومه الصّحيح والدِّفاع عنه والتصدي للأفكار الهدامة، ويعلوها نشر العلم الصّحيح المستمد من الكتاب والسنّة على فهم سلف الأمّة بوسائل مختلفة وفي مناطق متفرقة في البلاد.**

## أقسام المركز

**يشمل المركز عدّة أقسام منها:-**

- **مركز الهِداية لتعليم المهتدين الجدد**
- **معهد اللغة العربية والعلوم الشّرعيّة للبنات**
- **معهد دار الحديث لتدريب الدّعاة والمدرسين**

# نبذة تعريفية عن مركز ابن مسعود الإسلامي

بسْمِ اللهِ الرَّحمَنِ الرَّحِيمِ

الحمد لله رب العالمين، وصلى الله وسلم وبارك على محمد وعلى آله وصحبه، أما بعد:–

أُنشِئ مركز ابن مسعود الإسلامي في شهر شعبان سنة 1430 هـ بعد ماحصَل على شهادة الرّخصة كهيئة دينية من وزارة العدل الإثيوبي برقم 0034 تمكّنه من القيام بأنشطة دعويّة تخدم الإسلام والمسلمين بطرق منتظمة في مجالات كثيرة. فهو حافل بأنشطة علميّة مختلفة من الدّروس والمحاضرات والأنشطة الثقافية والندوات والمسابقات الدّينية والدّورات العلميّة وغيرها.

ለተሟላ ጥቅም ይህንንም ያንብቡ!!!

# የነብዩ ﷺ አሰጋገድ

## ከተክቢር እስከ ተስሊም

«አሰጋገዴን እንዳያችሁ ስገዱ፡፡» (ቡኻሪ ዘግበዉታል)

ዝግጅት፡- በሸይኽ ሙሀመድ ናስሩዲን አል-አልባኒ

ትርጉም፡- ኒዛሙዲን አወል

تلخيصُ صِفة صلاة النّبي ﷺ

من التكبير إلى التسليم كأنك تراها

«صلوا كما رأيتمُوني أصلي» رواه البخاري

إعداد: محمد ناصر الدين الألباني (رحمه الله تعالى)

ترجمة: نظام الدّين أوّل

أمهري – إثيوبيا